# አዲስ ዘመን

አንድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 355 ነሐሴ 25 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## “አሸባሪው ሕወሓት ሶስተኛ ዙር ጦርነት የከፈተው የትግራይ ሕዝብ እንደሚያጠፋው ስለተገነዘበ ነው”

- አቶ ከበደ ዴሲሳ

*የመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ*



ፎቶ- ከፋይል

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት ጦርነት የከፈተበት ምክንያት የማሸነፍ ዓላማ ይዞ ሳይሆን ከትግራይ ሕዝብ ጥያቄ ለመደበቅና ሕዝቡ እንደሚያጠፋው ስለተገነዘበ ነው ሲል የመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ፡፡

የመንግሥት ኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ከበደ ዴሲሳ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለመገናኛ ብዙኃን ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ አሸባሪው ሕወሓት ሶስተኛ ዙር ጦርነት የከፈተው ለማሸነፍ ዓላማ ይዞ ሳይሆን የትግራይ ሕዝብ እንደማያኖረውና እንደሚያጠፋው ስለተገነዘበ በጦርነት ውስጥ ተደብቆ ለማለፍ አስቦ ነው፡፡

የሽብር ቡድኑ በስሜን ዕዝ ጥቃት በሰነዘረበት ወቅት እንኳ ሁሉንም ነገር በተቆጣጠረበት ጊዜ ማሸነፍ ያልቻለ፤ ብዙ ሞክሮ ውርደትን ተከናንቦ እንደተሸነፈ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ መንግሥት

“አሸባሪው ሕወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# ቡድኑ ሕጻናትን በጦርነት በማሳተፍ የጦር ወንጀል ፈጽሟል

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎችን በመጣስ ሕጻናትን ለጦርነት በመመልመል የጦር ወንጀል እየፈጸመ መሆኑን የሕግ መምህርና ጠበቃ የሆኑት አቶ ቸርነት ሆርዶፋ ገለጹ።

አቶ ቸርነት ሆርዶፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የ1949ኙን የጄኔቫ ስምምነትን ጨምሮ በሌሎችም ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች ሕጻናትን ለወታደርነት መመልመል የጦር ወንጀል እንደተፈጸመ የሚያስቆጥር መሆኑ ተደንግጓል። አሸባሪው ሕወሓት ግን እነዚህን ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች በመጣስ ሕጻናትን በጦርነት እየማገደ ስለሆነ የጦር ወንጀል እንደፈጸመ ይቆጠራል።

ሕጻናትን በጦርነት ማሳተፍ በዓለም ላይ ችግር መሆኑ ታውቆ እኤአ በ1949 በጀኔቫ ስምምነት አንቀጽ 50 ላይ ሕጻናትን ለወታደርነት መመልመል ክልክል ነው ተብሎ ተደንግጓል ያሉት አቶ ቸርነት፤ ይህን ተከትሎ እኤአ በ1977 በወጡ የስምምነቱ ሁለት ፕሮቶኮሎች ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናትን ለውትድርና መመልመልም ሆነ ለግጭት መጠቀም ወንጀል ነው ተብሎ ተደንግጓል። በተጨማሪ በ1989 የወጣው የሕጻናት ኮንቬንሽን፣ የ1998ቱ የዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ ድንጋጌና የአፍሪካ ቻርተርን ጨምሮ በሌሎችም ዓለም አቀፍ ሕጎች ሕጻናትን ለወታደርነት መመልመል የጦር ወንጀል

ቡድኑ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ሕወሓት በርካታ ሕጻናትን ለጦርነት አሰልፏል



## የሕወሓት ሶስተኛ ዙር ጦርነት የከፈተው የታሪካዊ ጠላቶቻችንን ምኞት ለማሳካት ነው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት አሸባሪ ተብሎ የተፈረጀው የሕወሓት ቡድን ለሶስተኛ ጊዜ ጦርነት የከፈተው የታሪካዊ ጠላቶቻንን ምኞት ለማሳካት ነው ሲሉ የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ (አብን) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ጣሂር መሀመድ ገለጹ። የሀገር አንድነትና ሰላምን የማስጠበቅ ኃላፊነት ለመንግሥት ብቻ የሚተው ሳይተው ሁሉም ኃላፊነቱን ሊወጣ የሚገባበት ወቅት መሆኑንም ገልጸዋል።

አቶ ጣሂር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሕዝብ ትግል ከሥልጣኑ የተባረረው አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በተደጋጋሚ ለሰላም የተደረገለትን ጥሪ ባለመቀበል በታሪኩ ሰላምን እንዳማራጭ አድርጎ ያለማወቁን በተግባር አሳይቷል። በመሆኑም የሽብር ቡድኑ ፀብ የኢትዮጵያን ህልውና አደጋ ላይ የመጣል እንጂ ከመንግሥት ጋር ብቻ የመጣላት ጉዳይ አይደለም።

እስካሁን መንግሥት ሰላምን ለመከተል የሄደበት ርቀት የሚያስመሰግነው መሆኑን የገለጹት አቶ ጣሂር፤

የሕወሓት ሶስተኛ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## በዓልን ምክንያት በማድረግ ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ እንዳይደረግ ቁጥጥር እየተደረገ ነው

ገጽ 3

# “ግንባር በመዝመትም ሆነ በደጀንነት የአገራችንን ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ ዝግጁ ነን”

- የአዲስ አበባ ወጣቶች

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ግንባር ድረስ በመዝመትም ሆነ ለሠራዊቱ ደጀን በመሆን ለአገራቸው ሉዓላዊነት መረጋገጥ አስፈላጊውን ዋጋ ለመክፈል መዘጋጀታቸውን አስተያየታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሰጡ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ገለጹ።

ከአስተያየት ሰጪዎች መካከል የሆነችው ኃይማኖት ዝናቡ እንዳለችው፤ ቀደምት እናት አባቶቻችን ኢትዮጵያን ያስረከቡን በብዙ ዋጋና መስዋዕትነት ነው። በመሆኑም ለሦስተኛ ጊዜ የተፈጸመውን የአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ለመቀልበስ ግንባር ድረስ ከመዝመት ጀምሮ መከፈል ያለበትን ሁሉ ዋጋ በመክፈል የአገርን ነጻነትንና ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ ዝግጁ ነኝ ብላለች።

ኢትዮጵያ የበርካታ ወጣቶች አገር እንደመሆኗ የአገሪቱ ቀጣይ እጣ ፋንታ በወጣቶች ብርታት እንደሚወሰን አመልክታ፤ ወጣቶች ታምር መሥራት የሚችሉበትን ይህን እድሜያቸውን ለአገራቸው ሁለንተናዊ ሕልውናና ነጻነት መረጋገጥ ሊያውሉት እንደሚገባም ጠቁማች።

በጋራ ከቆምን የትኛውንም ጠላት የምናሸንፍበትን ኃይል እንጎናጸፋለን ያለችው ወጣቷ፤ ሁሉም ወጣቶች ኢትዮጵያዊነትን አስቀድመው ለሕልውናዋ መረጋገጥ በጋራ እንዲቆሙ ጥሪ አቅርባለች።

ወጣት እንደሻው ፈለቀ በበኩሉ፤ ወጣቱ የአገር ባለቤት ስለሆነ የዚችን አገር ሕልውና የማስጠበቅ ግዴታ አለበት ብሏል።

አሁን ላይ አገራችን በወረራ ውስጥ እንደምትገኝ አስታውሶ፤ ወጣቱ ይህን ወረራ ለመቀልበስ ከዚህ በፊት ሲያደርግ እንደነበረው በደጀንነትም ሆነ ግንባር ድረስ ተሰልፎ ለአገሩ ነጻነት ዘብ ሆኖ መቆም እንዳለበት አስገንዝቧል።

ወጣቶች ሕልማቸውን ሊያሳኩ የሚችሉት ነጻና አንድነቷ የተረጋገጠ አገር ሲኖር በመሆኑ ኢትዮጵያን ከተጋረጠባት አደጋ ለመታደግ ጊዜ መስጠት እንደሌለባቸው ጠቁሟል።

የአገር ሰላም የሚረጋገጠው ሁሉም ዜጋ በየአካባቢው ከሚያደርገው ንቁ አገራዊ እንቅስቃሴ መሆኑን ጠቁሞ፤ በተለይ ወጣቱ ለአገር ሰላም መረጋገጥ ለአፍታም ቢሆን ቸል ማለት እንደሌለበት አስረድቷል።

ሌላኛዋ አስተያየት ሰጪ ወጣት አስናቀች ግዛው እንደገለጸችው፤ ወጣቱ እንደ አገር ያሉ መልካም አጋጣሚዎችን ተጠቅሞ አገሪቱን ወደፊት የማሻገር ኃላፊነት አለበት።

በተለይ አሁን የምንገኝበት ወቅት ኢትዮጵያ በአሸባሪው የሕወሓት ቡድን ዳግም ወረራ የተፈጸመባት መሆኑን አስታውሳ፤ ወጣቶች በጋራ በመቆም ቡድኑ ኢትዮጵያ ለማፍረስና የትግራይን ሕዝብም ከኢትዮጵያውያን ለመነጠል የሚያደርገውን እኩይ ጥረት ማክሸፍ አለብን ብላለች።

እንደአገር የተፈጸመውን ወረራ ለመቀልበስና የኢትዮጵያን ሕልውና ለማረጋገጥ ለአገር መከላከያ ሠራዊቱና ለአገር ነጻነት ዋጋ እየከፈሉ ለሚገኙ ኃይሎች ደጀን ከመሆን እስከ እስከ መዝመት የሚደርስ ቁርጠኝነት እንዳላትም ወጣት አስናቀች ጨምራ ገልጻለች።

ያለችን አንድ አገር ናት ያለችው ወጣት አስናቀች፤ የትግራይን ሕዝብ ጨምሮ ዋጋ እየከፈለ ያለው የራሳችን ወገን ስለሆነ በኢትዮጵያዊነት የአሸናፊነት ወኔ በመነሳት ዛሬውኑ ኃላፊነታችንን እንወጣ ስትልም መልእክቷ አስተላልፋለች።

ወጣት ሰጠኝ መላክ እንደሚለው ደግሞ፤ ከዚህ በፊት የተፈጸሙ ወረራዎችን ለመቀልበስ ደም በመለገስ፣ ስንቅ በማዘጋጀትና ሌሎችንም የደጀንነት ሥራዎች ላይ ተሳትፏል።

ጦርነት ባይፈለግም ገፍቶ ከመጣ ወጣቱ አገርን ከጥቃት የመከላከል ግዴታ እንዳለበት ጠቁሞ፤ በነጻነት የተረከብናትን አገር ነጻነቷን ጠብቃ እንድትቀጥል ለማድረግ ሁሌም ዝግጁ መሆን አለብን ብሏል።

ጠላትን ድል ማድረግ የሚቻለው በትብብር ስለሆነ ወጣቱ በሃይማኖትም ሆነ በጎሳ ከመለያየጥት ወጥቶ በተባበረ ክንድ ለአገሩ ዘብ መቆም እንዳለበት አመላክቷል።

# “ፀረ ሰላም ሃይሎችን እምቢ ልንላቸውና ልናወግዛቸው ይገባል”

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ጥላቻና ጦርነት የሚሹ ፀረ ሰላም ኃይሎችን እምቢ ልንላቸውና ልናወግዛቸው ይገባል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ።

የአሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይ እና ሶለል በዓል የማጠቃለያ መርሐ ግብር ትናንትና ሲከናወን ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፤ ጥላቻና ጦርነት ፈላጊውን አሸባሪ የሕወሓት ቢድን ማውገዝ ይገባል።

የአሸንዳ በዓል ማጠቃለያ ስናከብር ጦርነት አውግዘን ሰላም መሻታችን የምናሳይበት ነው። አጥፊዎችም እኩይ ዓላማቸውን ሊያቆሙ የሚገባበት ጊዜ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

የአሸንዳ በአል የሰላም አንድነትና መተባበር ማሳያ በመሆኑ ኢትዮጵያም ሰላም ትሻለች ጦርነት ታወግዛለች ብለዋል።

የአሸንዳ በዓል ለሴቶች ተፈጥሮ የቸረቻቸውን ፀጋ የሚገልፁበት በዓል ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ አሸንዳ በማሕበረሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ ህፀፆች የሚወገዱበት ሰላም ወዳድነት ጎልቶ የሚስተዋልበትና ሰላምን የሚሰብክ በዓል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አሸንዳ ሴቶች ሃሳባቸውን በነፃነት በመግለፅ የውስጣቸውን አቅም የሚያሳዩበት በዓል መሆኑን ያነሱት ከንቲባ አዳነች፤ የማሕበረሰቡ እሴቶች ጎልተው የሚወጡበት የአሸንዳ በዓል ሲከበር ስለሰላም አብዝተን ልንናገርና ልንሰብክ ይገባል ብለዋል።

በክብረበዓሉ ላይ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤን ጨምሮ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ቀጀላ መርዳሳና ኮማንደር አትሌት ደራርቱ ቱሉ እንዲሁም የፌዴራልና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

በማጠቃለያ መርሃ ግብሩ ላይ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል የተሰባሰቡ ብሄር ብሄረሰቦችም በዓሉን በአንድነት ያከበሩ ሲሆን፤ ከሁሉም የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች የተውጣጡ ልጃገረዶች በተለያዩ ባህላዊ አልባሳት አጊጠው በዓሉን አድምቀዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች ከነሐሴ 16 ቀን ጀምሮ በተለያዩ ሥነ ሥርዓቶች ሲከበር የቆየው የአሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይ እና ሶለል በዓል የማጠቃለያ መርሐ ግብሩ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ተከናውኗል።

የ2013 ዓ.ም የአሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ሻደይ እና ሶለል በዓል የማጠቃለያ መርሐ ግብር በአዲስ አበባ ወዳጅነት ፓርክ መከበሩ የሚታወስ ነው።



# የጠላትን ሴራ በመመከት ለሕዝቦች ሰላምና አንድነት በትብብር መስራት ያስፈልጋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የጠላትን ሴራ በአስተማማኝ ደረጃ በመመከት ለሕዝቦች ሰላምና አንድነት በትብብር መስራት እንደሚገባ የደቡብ እና የኦሮሚያ ክልሎች ከፍተኛ የሥራ አመራሮች ገለጹ።

የደቡብ እና የኦሮሚያ ክልሎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በወቅታዊ የጸጥታ ጉዳዮች ላይ በሃዋሳ ከተማ ሲመክሩ የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳ፤ በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልል አዋሳኝ አካባቢዎች ዘላቂ ሰላም ለማስፈን በትብብር መስራት የሚያስችል መድረክ መሆኑን ገልጸዋል።

በሁለቱም ክልል የሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ደህንነት ማስጠበቅ የመንግሥት አብይ ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይ የጠላትን እኩይ ተግባር በማክሸፍ ሰላም ማስፈን ይገባል ነው ያሉት።

በደቡብ እና በኦሮሚያ ክልሎች የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን በማጎልበት የቀጠናውን ሰላም በአስተማማኝ ደረጃ ለማስፈን እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

በኦሮሚያ ክልል በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የከተማ ልማት ክላስተር አስተባባሪ አቶ አዲሱ አረጋ በበኩላቸው፤ የውስጥ እና የውጭ ጠላቶች የከፈቱትን ዘርፈ ብዙ ወረራ በመመከት የዜጎችን ደህንነት ለማስጠበቅ እየተሰራ ነው ብለዋል።

የሸኔ እንቅስቃሴ ባለባቸው አካባቢዎች መጠነ ሰፊ ዘመቻ በማድረግ የሽብር ቡድኑን የማጽዳት ስራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፤ የሕዝቡን ሰላም ለማስፈን የተጀመረው ጥረት ስኬታማ ነው ብለዋል።

በሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች ዘላቂ ሰላም በማስፈን የተጀመረውን ልማት ማስቀጠል ይገባልም ነው ያሉት።

አሸባሪው ሕወሓት የሚጋልበው ሸኔ እና የውጭ ጠላቶቻችን ሀገሪቱን የትርምስ ቀጠና ለማድረግ እያካሔዱት ያለውን ሴራ በብቃት የመመከት ስራ እየተሰራ መሆኑንም አብራርተዋል።

በውይይት መድረኩ ከደቡብ እና ከኦሮሚያ ክልሎች የተውጣጡ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች መገኘታቸውን ከደቡብ ክልል ኮሙኒኬሽን የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ዜና

# በዓልን ምክንያት በማድረግ ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ እንዳይደረግ ቁጥጥር እየተደረገ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- መጪውን የአዲስ ዓመት በዓል ምክንያት በማድረግ ሊደረጉ የሚችሉ ያለአግባብ የሆኑ የዋጋ ጭማሪዎች እንዳይከሰቱ ቁጥጥር እያደረገ መሆኑን የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አስታወቀ። ቢሮው የአቅርቦት ማነስና የዋጋ መጨመር ችግሮችን በፍጥነት ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት ላይ እንደሚገኝም አሳውቋል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ቢሯቸው የአዲስ ዓመት በዓል አከባበር ጋር ተያይዞ ሊመጡ የሚችሉ የዋጋ ልዩነቶችን ለማርገብና የተረጋጋ የገበያ ግብይት እንዲኖር ሲባል ቅድመ ዝግጅት አድርጓል።

በዓሉን ተከትለው ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር እና ሥርዓት ያለው የዋጋ ግብይት እንዲፈጠር ሲባል ግብረ ሃይል ተዋቅሮ እየተሰራ እንደሆነም አቶ አደም ጠቁመዋል።

የአዲስ ዓመት በዓልን መሰረት አድርገው ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ አካላትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ግብረ ሃይል ኮሚቴ ተዘጋጅቷል ያሉት ኃላፊው፣ የአቅርቦት፣ የንግድ ቁጥጥርና የኮሙኒኬሽን በሚል በሦስት ንኡስ የተዋቀረ ኮሚቴ ነው ብለዋል። ኮሚቴውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ የሚመራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ አደም ገለፃ፣ አብዛኛውን ጊዜ የዋጋ ጭማሪ የሚደረገው የአቅርቦት እጥረት ባለባቸው ምርቶች ላይ ነው። የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ምርቶች በፍጥትና በተመጣጣኝ ዋጋ በሸማች ሕብረት ስራ ማሕበራት በኩል ለሕብረተሰቡ ለማቅረብና የአቅርቦት እጥረት እንዳይከሰትም እየሰራ እንደሆነ ተናግረዋል።

አሁን ላይ ከከተማ እስከ ወረዳ ድረስ በሕግ ማስከበርና በአቅርቦት ክትትል ላይ የሚሰሩ ተቋማት የተወከሉበት ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ስራ ገብቷል ያሉት አቶ አደም፣ ኮሚቴው የአቅርቦት እጥረትና የዋጋ ጭማሪ እንዳይፈጠር አምራች ማሕበራት ምርታቸውን በቀጥታ ለሸማቹ የሚያቀርቡበት መንገድ እያመቻቸ ይገኛል ብለዋል።


አቶ አደም ኑሪ

በዚህም በእህልና ጥራጥሬ፣ በእንስሳትና በእንስሳት ተዋጽኦ እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬ ከሚያቀርቡ አካላት ጋር ትስስር እየተፈጠረ ነው። እነዚህ ምርቶች በሚቀርቡበት አካባቢዎች የተቋቋመው ኮሚቴ እንደሚገኝም ኃላፊው ተናግረዋል።

ኮሚቴው ያመጣው ዘይትና ስኳር እንዲሁም ሌሎች ምርቶች በትክክል ለሕብረተሰብ መድረሳቸውን እንዲሁም ለሕገወጥ ተግባራት ተጋላጭ እንዳይሆኑ የማድረግ ተግባርን እንደሚያከናውን ኃላፊው አስታውቀው፣ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በአገር ውስጥ ፋብሪካዎች አማካኝነት የሚመረት ዘይትን እንዲሁም ከውጭም የሚገባውን ወደ ሕብረተሰቡ እንዲደርስ በትኩረት ስራዎቹን እንደሚሰራ አስረድተዋል።

የኮሚቴው ዋንኛ ተግባር ሕግ የማስከበር እንዲሁም አቅርቦት ችግር እንዳይከሰት መቆጣጠር ነው ያሉት አቶ አደም፤ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ መሰል የሕግ ማስከበር ተግባራትን እንደሚቀጥልም አቶ አደም ኑሪ ገልጸዋል።

በገበያ ውስጥ ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ የኑሮ ውድነት እንዲባባስ የሚያደርጉ ሕገ ወጥ ደላሎች ይገኛሉ ያሉት ኃላፊው፣ ሕገ ወጥ የደላላ ሰንሰለቱን በመቁረጥ የኑሮ ውድነትን በዘላቂነት ለመቅረፍ ቢሮው በልዩ ትኩረት እንደሚሰራ ተናግረው፣ ቢሮው ከመደበኛ የንግድ ሥርዓት ባሻገር የተለያዩ ወቅታዊ የሆኑ የንግድ ሥርዓቶችን እያመቻቸ ይገኛል ብለዋል።



## “የአንድነት ቀን”
## በመላ አገሪቷና የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በሚገኙበት ሁሉ ይከበራል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- “የአንድነት ቀን” በሚል የተሰየመው ጳጉሜን 5 ቀን 2014 ዓ.ም በመላው ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በሚገኙበት በታላቅ ድምቀት እንደሚከብር የበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴ ገለጸ።

የበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት የመከላከያ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ዋና ዳይሬክተር ኮ/ል ጌትነት አዳነ ፤ በዓሉ በተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚከበርና አስታውቀዋል።

“ተፈጥሯዊ የሆነውን ልዩነቶቻችን እንደ ችግር ለመጠቀም የሚፈልጉ የውጭና የውስጥ የሀገራችንን ጠላቶች በተለመደው ኢትዮጵያዊ አንድነታችን በመቆም ለዓለም የምናሳይበት በዓል ይሆናል” ብለዋል።

በዓሉ ከግለሰብ ጀምሮ በተለያዩ ተቋማት ደረጃ በታላቅ ድምቀት እንደሚከበርና አዲሱን ዓመት በአዲስ ተስፋ ለመቀበል የምንነሳሳበትና የአንድነት መገለጫ የሆነው ጀግናው የመከላከያ ሠራዊታችንን የምናከብርበት ዕለት ይህናል ሲሉ ኮሎኔል ጌትነት አዳነ ገልጸዋል።

የመንግሥት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዳይሬክተር ጄኔራል አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ፤ በዓሉ ከሀገር ውጭ በሃምሳ ሁለት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንሲላ ፅ/ቤቶች በድምቀት እንደሚከበር ገልጸዋል።

በዕለቱ ሀገራዊ አንድነትን የሚያጎሉ የተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚደረጉና አምስት ሰዓት ላይ “እኔ ለሀገሬ አንድነት” የሚል ልዩ ፕሮግራምም መሰናዳቱን የሀገር መከላከያ ሠራዊት በማህበራዊ ገጹ አስታውቋል።

## በጦርነት ወቅት በሃሰት መረጃዎች እንዳንወናበድ ከአንድ ማዕከል የሚወጡ የመንግሥት መረጃዎችን መጠቀም ይገባል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- በጦርነት ወቅት በሃሰት መረጃዎች እንዳንወናበድ ከመንግሥት አካላት የሚሰጡ የአንድ ማዕከል መረጃዎችን ብቻ ልንጠቀም ይገባል ሲሉ በዲላ ዩኒቨርሰቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን መምህርና የዶክትሬት ዲግሪ ተማሪው አቶ አለበል ጓንጉል ገለጹ።

አቶ አለበል ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጹት፤ በጦርነት ወቅት መረጃን ከሚመራ አካልና ታማኝ ከሆኑ የመንግሥት መገናኛ ብዙሃን ብቻ መውሰድ አስፈላጊ ነው። መገናኛ ብዙሃንም ለሕዝብ የሚሰጡትን መረጃ በጥንቃቄና ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ በወቅቱ ሊሰጡ ይገባል። ምክንያቱም የጦርነትና የቀውስ ጊዜ ኮሙዩኒኬሽን ጥንቃቄ በተሞላበት ሊከናወን ይገባል። በዚህ ጊዜ የአገርን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ መረጃዎች ሊተላለፉ ስለሚችሉ ከመቼው ጊዜ በበለጠ በጥንቃቄ መስራት ተገቢ ነው።

በአሁኑ ወቅት የማሕበራዊ ሚዲያዎች በርካታ ተከታይ እንዳላቸው ይታወቃል ያሉት አቶ አለበል፤ ነገር ግን በርከት ያለ ተከታይ ያላቸው የማሕበራዊ ሚዲያዎችና አንቂዎች ሁሉ ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ ማለት እንዳልሆነ በመገንዘብ ሕብረተሰቡ ከዚህ ውዥንብር እንዲወጣ መረጃውን ከማን ነው መውሰድ ያለብኝ፣ መረጃን የሚሰጡ አካላት ከዚህ በፊት የሚሰጡት መረጃ ትክክለኛነት ምን ያህል ነው፣ የሚለውን ማረጋገጥ መቻል አስፈላጊ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ አለበል ገለጻ፤ መረጃ የሚሰጡ አካላትም ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ እንዳይሰጡ ከሚመለከተው አካል ማሳሰቢያ ሊሰጣቸው ይገባል፤ ማሕበረሰቡም መረጃ ከየትና ከማን መውሰድ እንዳለበት መገናኛ ብዙሃን በተከታታይ ማሕበረሰቡን የማስገንዘብ ስራ ሊሰሩ ይገባል።

በአንጻሩ በጦርነት ወቅት ሕዝብ ለሀሰተኛ መረጃ እንዳይጋለጥና መደናገር እንዳይኖር ከአንድ ማዕከል የሚሰጥ መረጃ ሊኖር እንደሚገባም አቶ አለበል ጠቁመዋል።

አቶ አለበል እንዳሉት፤ በጦርነትና በቀውስ ጊዜ አንድ ሀገር ሊከተለው የሚገባ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ አለ። ይህም ወቅቱን የጠበቀ መረጃ በአንድ የኮሙዩኒኬሽን ሰንሰለት መስጠት ነው። ለዚህም በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽንና የአገር መከላከያ ሠራዊት ትልቅ ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት ናቸው። የመከላከያ ሠራዊት የኮሙዩኒኬሽን ዘርፉና የመንግሥት ኮሙኒኬሽን በአንድ ማዕከላዊ ዕዝ በመሆን ተናበው በየጊዜው ለሕዝቡ መረጃዎችን ማድረስ ይጠበቅባቸዋል።

“መረጃ የሚፈልገው ማሕበረሰብ በጣም ብዙ ነው። ስለዚህ መረጃ በአግባቡ ሳይሰጥ ሲቀር ሕብረተሰቡ ለተለያዩ የሀሰት መረጃዎች ሰለባ ይሆናል። ይህን የመረጃ ፍላጎት በተገቢው መንገድና ወቅቱን በጠበቀ መንገድ መስጠት


አቶ አለበል ጓንጉል

ይገባል። ለዚህ ደግሞ አንድ ወጥ የሆነ ማዕከላዊ የሆነ የመረጃ አሰጣጥ መዘርጋት ወሳኝ ነው” ብለዋል።

እንደ አቶ አለበል ገለጻ፤ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃንና አንዳንድ የማሕበራዊ ሚዲያዎች የመገናኛ ብዙሃን አሰራርና የሙያ ሥነምግባሩን በመጣስ ያልተገባና ሀሰተኛ መረጃ እያሰራጩ ሕዝብ እያደናገሩ ነው። መደናገሩን ለመግታት የተደራጀ፣ የተቀናጀና ከአንድ የመረጃ ቋት የሚሰጥ መረጃ መኖር አስፈላጊ ነው። ለሀሰተኛ ዘገባዎች ምላሽ እየሰጡ መቀጠል ሳይሆን የመረጃ ምንጫቸው ለመሆን መስራት ያስፈልጋል።

ባለፈው ዓመት የነበረው የኮሙዩኒኬሽን ሥርዓት የወረዳ ኮሙዩኒኬሽን ሳይቀር መረጃ ሲሰጥ እንደነበር አስታውሰው፤ ይህም መረጃ ወጥነትና ከሌሎች የኮሙዩኒኬሽን መረጃ ልዩነት ያለው ስለነበር ሕዝብ እንዲደናገር በር ከፍቶ ተስተውሏል ብለዋል። “መረጃው በዋናነት ከአንድ ማዕከል ሊሰጥ የሚችልበት መዋቅር መኖር አለበት። አሁን የመረጃ አሰጣጡ በተወሰነ መንገድ መሻሻሎች አሉ። ይህም ወጥ በሆነ መንገድ መቀጠል አለበት” ሲሉም ተናግረዋል።

ባለፈው የግጭት ወቅት የተለያዩ አክቲቪስቶች በኩል ሰበር ዜና እያሉ “እዚህ ቦታ በእከሌ ተያዘ፣ ይህንን አካባቢ ይህ ሃይል ተቆጣጠረ፤ ወዘተ” እያሉ የተሳሳተ መረጃ በመንዛት ሕብረተሰቡ ውዥንብር ውስጥ እንዲገባ ሲያደርጉ እንደነበር የጠቆሙት አቶ አለበል፤ የማሕበራዊ ሚዲያ ተከታይን ቁጥር ለማብዛት ሲሉ ብቻ አገር የሚያተራምሱ በርካታ የማሕበራዊ ሚዲያ አወናባጆች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

መረጃ የሚሰጡ አካላት ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ እንዳይሰጡ ከሚመለከተው አካል ማሳሰቢያ ሊሰጣቸው ይገባል ያሉት አቶ አለበል፤ ማሕበረሰቡም መረጃ ከየትና ከማን መውሰድ እንዳለበት መገናኛ ብዙሃን በተከታታይ ማሕበረሰቡን የማስገንዘብ ስራ ሊሰሩ ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል።

# ለጤና መድህን አገልግሎት የሚሰበሰበው መዋጮ በባንክ ሥርዓት ውስጥ ሊያልፍ ነው

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ለጤና መድህን አገልግሎት ሲባል ከማሕበረሰቡ የሚሰበሰቡ መዋጮዎች በባንክ ሥርዓትና በሌሎች አማራጭ የፋይናንስ አገልግሎት ተቋማት ውስጥ እንዲያልፉ እየተሰራ መሆኑን የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት የፋይናንስ ተቋማት በተለይም ባንኮች በጤና መድህን ሥርዓት ወስጥ ያለውን የገንዘብ አሰባሰብ ስልት ዘመናዊ ለማድረግ ሚናቸው የጎላ በመሆኑ በዘርፉ የራሳቸውን አስተዋፅኦ እንዲወጡ ለባንክ አመራሮች የግንዛቤ መፍጠርና ያሉ እድሎችን የማስተዋወቅ መርሃ ግብር ተካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ፍሬህይወት አበበ በዚህ ወቅት እንዳስታወቁት የጤና መድህን ዋነኛ ዓላማ መዋጮዎችን በመሰብሰብ ዜጎች ህክምና በሚፈልጉበት ወቅት ያላንዳች ተጨማሪ ወጪ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑን አንስተው፣ ከአባላት የሚሰበሰቡ መዋጮዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ በበምጣታቸው ምክንያት ከዚህ በፊት በእጅ የሚሰበሰቡ መዋጮዎች በባንክ ሥርዓት ውስጥ እንዲያልፉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

መዋጮዎች በሚሰበሰቡበት ወቅት በባንክ ሥርዓት እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲሁም ዜጎች በአንድ ጊዜ የሚከፍሉትን መዋጮ ረዘም ባለ ጊዜ በባንኮች በመቆጠብ በአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ለመፍጠር ያለመ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የማሕበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን በሁሉም ክልሎች እየተተገበረ እንደሆነና በዚህም ከ9.8 ሚሊዮን በላይ እማዋራ/አባወራዎች የጤና መድህን ሥርዓት አባል መሆናቸውን የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሙሉቀን አርጋው ለተሳታፊዎች ባቀረቡት ፅሁፍ ገልፀዋል፡፡

በዚህም አጠቃላይ የተጠቃሚዎች ቁጥር ወደ አርባ አምስት ሚሊዮን መድረሱንና ከዚህም ስምንት ሚሊዮን የሚደርሱ የማህበረሰብ ክፍሎች የመክፈል አቅም የሌላቸው በመሆኑ በመንግሥት ተሸፍኖ ተጠቃሚ እንደሆኑ ዶክተር ሙሉቀን ተናግረዋል፡፡

የገጠር ማሕበረሰብ 375 ብር፣ የገጠር ከተሞች ለሚኖሩ 500፣ ትልልቅ ከተሞች 665 ብር እንዲሁም ለአርብቶ አደር አካባቢዎች 325 ብር መዋጮ ተተምኖ እየተሰበሰበ ሲሆን ከዚህም ሶስት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር የተሰበሰበ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከመድኃኒት አቅርቦት ጋር ተያይዞ የጤና መድህን ተጠቃሚዎች ህክምና ከተሰጣቸው በኋላ መድኃኒቶችን በገንዘባቸው ከውጭ እንዲገዙ የሚገደዱ በመሆኑ በዚህ ረገድ በየወቅቱ የሚነሱ ችግሮችን በማስመልከት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የገለጹት ዋና ዳይሬክተሯ፣ እንደ ሀገር የመድኃኒት አቅርቦት ችግር፣ የህክምና ተቋማት አስፈላጊ የሆኑ መድኃኒቶችን በበቂ ሁኔታ ያለመያዝ እንደ ዋነኛ ማነቆ መሆናቸውን አንስተዋል፡፡

ለዚህም ከሶስት መቶ በላይ የመድኃኒት አቅራቢ ተቋማት ጋር በተለይም የከነማና ቀይ መስቀል መድኃኒት ቤቶች ጋር ውል በመግባት ለነዚህ ተጠቃሚዎች መድሃኒት እንዲያቀርቡ እየተደረገ መሆኑን ተናግረው፣ ከግል ተቋማት ጋር ደግሞ በአነስተኛ ትርፍ ለተጠቃሚዎች መድኃኒቶችን የሚያቀርቡበት መንገድ እንደሚዘጋጅ ገልጿል፡፡

# ቡድኑ ሕጻናትን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደተፈጸመ የሚያስቆጥር መሆኑ ተደንግጓል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም የመን፣ ኡጋንዳ፣ ጎንጎ፣ ኮሎምቢያን ጨምሮ በብዙ አገራት ላይ ድርጊቱ መፈጸሙን አስታውሰው፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤትም ጉዳዩ ስላሳሰበው ብዙ ጊዜ የውሳኔ ሃሳብ ሰጥቷል ብለዋል።

አሁን ላይ አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ሕጻናትን በጦርነት በማሳተፍ እነዚህን ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች እየጣሰ ስለሆነ የጦር ወንጀል እንደፈጸመ ይቆራል ያሉት ባለሙያው፤ ኢትዮጵያም የአሸባሪው ቡድን አባላትን በጦር ወንጀል መክሰስ እንደምትችል ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ቸርነት ገለጻ፤ ምዕራባውያን አገራት ሁልጊዜም የሚከተሉት ብሔራዊ ጥቅማቸውን ስለሆነ የሚያስጨንቃቸው በእያንዳንዱ አገር የሚመጣው ሥርዓት ለእነርሱ የሚጠቅም ፖሊሲ የሚያወጣና የእነርሱን ዘላቂ ጥቅም የሚያስከብር መንግሥት እንዲኖር ማድረግ ነው። ይህም በመሆኑ እነርሱ ድጋፍ የሚሰጧቸው ቡድኖች የሚፈጽሙትን የጦር ወንጀልና የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳላዩ ያልፉታል።

ለእነዚህ አገራት የሰብኣዊ መብት ጉዳይ አጀንዳቸው የሚሆነው አገሩን የሚወድ፣ አገሩን ሚያከብርና ሕዝብን ከችግር ለማውጣት የሚፈልግ መንግሥት በየትኛውም አገር ላይ ሲመጣ መሆኑን አውስተው፤ የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ዓለምን የሚያዘናጉበት፣ በሰው አገር ጣልቃ ገብተው የሚፈልጉትን መንግሥት ለመመስረት የሚጠቀሙበት መሳሪያ እንጂ የቆሙለት ዓላማ ስላልሆነ አሸባሪው ሕወሓት ሕጻናትን በጦርነት ሲማግድ እያዩ እንዳላዩ በቸልታ ማለፍን መርጠዋል ብለዋል።

የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት እገታ ውስጥ በመሆኑ እነዚህ ለጋ ሕጻናት ወደ ጦርነት እየተማገዱ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንድ የትግራይን ሕዝብ ነጻ ለማውጣት መሥራት አለብን ያሉት ባለሙያው፤ ያልተቋረጠ ዓለም አቀፋዊ ንቅናቄ በመፍጠር እውነቱ በዓለም መድረክ እንዲገለጽና እየተፈጸመ ያለውን የጦር ወንጀል እንዳላዩ የሚያልፉትን ምዕራባውያን መንግሥታት ላይ ጫና እንዲደርስ ማድረግ እንደሚገባም አመልክተዋል።

# የሕወሓት ሶስተኛ ዙር ጦርነት የከፈተው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሕወሓትን የማስቆም ኃላፊነት የሁሉም ዜጋ እንጂ የመንግሥት ብቻ አለመሆኑንም ነው ያሰመሩበት። በመንግሥት በኩል በቅድሚያ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነቱን ሊወጣ እንደሚገባውም ነው አቶ ጣሂር በማከል የገለጹት።

እንደ አቶ ጣሂር ገለፃ፤ የሰላምን አማራጭ መጠቀም የማያውቀው የሕወሓት ሃይል ጥያቄና ቅሬታ ከመንግሥት ጋር ብቻ ሳይሆን ሀገርን የማፍረስና የኢትዮጵያን ህልውና አደጋ ላይ የመጣል ጭምር ነው።

ሀገራችን ባለችበት ከባድ ምስቅልቅልና ኢኮኖሚያዊ ጫና ላይ የሕወሓት ሰላምን ያለመፈለግ አባዜ ወቅታዊ ሁኔታዋ ላይ እንደጣላት የጠቆሙት አቶ ጣሂር፤ የሽብር ቡድኑ ካጠፋቸው ጥፋቶች ሁሉ በኋላ መንግሥት በብዙ ጫናዎች ውስጥ የሰላም ፍላጎትን ቢያሳይም ቡድኑ እምቢተኛነቱን መቀጠሉንና ወረራ መፈፀሙንም ነው የገለጹት።

ለሽብር ቡድኑ አሰቃቂ ወንጀሎች አዲስ አይደለንም፤ በታሪክ የሰራቸውን ግፎች እናውቃቸዋለን ያሉት አቶ ጣሂር የሕወሓት ሽብር ቡድን በርካታ ሕፃናትና አረጋውያንን በአሰቃቂ ሁኔታ ለጦርነት እያሰለፈ ጸረ ሰላምና የጦር አዋጅ ጎሳሚነቱን መቀጠሉንም ነው የገለጹት።

ሀገራችን በመንግሥትና ሕወሓት መሀል ባለችበት ወቅታዊ ሁኔታ ከሕዝቧ፣ ከታዋቂ ሰዎች ከፖለቲካ ፓርቲዎች ምን ይጠበቃል የሚለው ጉዳይ ላይም አስተያየታቸውን የሰጡት አቶ ጣሂር ሕዝቡ ይሄን ወቅት ተረጋግቶና በሀገራዊ አንድነት ሊያሳልፍ እንደሚገባ ገልጸዋል። አርቲስቶች ታዋቂ ሰዎችና የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች በመተባበርና በአንድነት በመቆም ሕዝቡን ማሳወቅ፣ ማንቃትና ማረጋጋት እንዳለባቸውም ተናግረዋል።

ወቅቱ ከዚህ በፊት እንደተደረገው ሁሉ ዜጎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ውዥንብር የሚለቀቅበትና ሕዝብን ወደ አለመረጋጋት የሚመራበት ሊሆን እንደሚችል የገለጹት አቶ ጣሂር፤ የሀገር አንድነትና ሰላምን የማስጠበቅ ኃላፊነት ለመንግሥት ብቻ ሳይተው እኔን አይመለከተኝም ሳይባል ሁሉም የየራሱን ኃላፊነት ሊወጣ የሚገባበት ወቅት መሆኑንም ነው የገለጹት።

አቶ ጣሂር የሽብር ቡድኑን አረመኔያዊ ድርጊት ባሳለፈው ጦርነት በአማራ እና አፋር ክልሎች የሚኖሩ በርካታ ንፁሃን ዜጎችን ሕይወትን በማጥፋትና ዘር ፍጅት ማድረጉንም አውስተዋል።

# “አሸባሪው ሕወሓት ሶስተኛ ዙር ጦርነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከጦርነት ይልቅ በንግግር ለመፍታት ተመራጭ ነው ብሎ ያቀረበውን የሰላም አማራጭ አሻፈረኝ ብሎ ጦርነት የከፈተው የማሸነፍ ዓላማ ይዞ ሳይሆን ከትግራይ ሕዝብ ጥያቄ ለመደበቅና ሕዝቡ እንደሚያጠፋው ስለተገነዘበ ነው ብለዋል፡፡

የሽብር ቡድኑ ለጀመረው ይፋዊ ወረራ መንግሥት እስካሁን ድረስ ከመመከት ያለፈ የማጥቃት እርምጃ አልወሰደም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ አሁንም ቡድኑ ወደ ሰላም እንዲመለስ ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ በቡድኑ ላይ ጫና ማድረግ እንደሚኖርበት ጠይቀዋል፡፡

በሌላ በኩልም የ2015 ዓ.ም የዘመን መለወጫ በዓልን ምክንያት በማድረግ ካለፉ ችግሮች ለመማርና የነበሩ ስኬቶችን አጠናክሮ ለማስቀጠል አምስቱ የጳጉሜን ቀናት በተለያዩ መርሀ ግብሮች ተከብረው እንደሚውሉ የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ከበደ ደሲሳ ፤ አምስቱ የጳጉሜን ቀናት ጳጉሜን_በመደመር በሚል መሪ ቃል ተከብረው እንዲውሉ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መወሰኑን ተናግረዋል።

ለአምስቱ ቀናት የተለያየ ስያሜ እንደተሰጣቸው የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በዚህም መሰረት፡- ጳጉሜ 1 የበጎ ፈቃድ ቀን፤ ጳጉሜ 2 የአምራችነት ቀን፤ ጳጉሜ 3 የሰላም ቀን ፤ ጳጉሜ 4 የአገልጋይነት ቀን እና ጳጉሜ 5 የአንድነት ቀን ሆኖ ተከብሮ እንደሚውል ጠቅሰዋል፡፡

በእያንዳንዱ የጳጉሜን ቀናት ከቀናቱ ስያሜ ጋር የተገናኙ መርሐ ግብሮች እና ተግባራት ይኖራሉ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ጷጉሜ አንድ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ባህል እየሆነ የመጣውንና ከፍተኛ ውጤት የተገኘበት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እሴትን ይበልጥ ለማጠናከር በሚያስችል መልኩ በተለያዩ መርሃ ግብሮች ታስቦ ይውላል፤ በተለይ እለቱ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክት እንዲሳካ ያደረገ፣ በዙ አቅመ ደካሞችን የቤት ባለቤት ያደረገ፣ በደም ዕጦት ሲያልፍ የነበረውን ሕይወት ለመታደግ ያስቻለ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራን ይበልጥ ባህል በሚያደርጉ ተግባራት ይከበራል ብለዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ ጷጉሜ አምስት የአንድነት ቀን መከበር ሲሆን ዓላማውም ለዘመናት የቆየው የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነትን ለማስከበር የተከፈለውን መስዋዕትነት በመዘከር ፤ አሁንም አገራችን ፈተናዎችን እየተሻገረች አንድነቷን ጠብቃ እየተጓዘች እንዳለች እና ቀጣይም በልጇቿ መስዋዕትነትና ጥረት አንድ ሁና እንደምትቀጥል ለማሳየት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ዛሬም በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እንገኛለን፣ ለታሪካዊ ጠላቶቻችን የሚላላኩ በአሸባሪው ወያኔ ለ3ኛ ጊዜ የተወረርንበት ጊዜ ውስጥ እንገኛለን ያሉት አቶ ከበደ፤ ይህንን ወረራ በድል የምናጠናቅቀውና ዘላቂ ሠላማችንን የምናረጋግጠው አንድነታችንን በማጠናከር ብቻ ነው ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ በአዲሱ ዓመት ዋዜማ 5ቱ የጳጉሜ ቀናት በፌዴራል፣ እንዲሁም በክልሎችና በከተማ መስተዳድሮች በተመሳሳይ ስያሜ እንደሚከበሩ አመልክተው፤ የክልልና ከተማ መስተዳድሮች እንደየክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ የቀናቱን ስያሜና ዓላማን ተከትለው እንደሚያከብሩ እና በየደረጃው ያሉት የመንግሥት ተቋማትም በየተቋማቸው እንደየነባራዊ ሁኔታቸው የሚያከብሩ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው 2014 ዓ.ም ፈተናዎች የበዛበት፥ ነገር ግን በበርካታ አኩሪ ድሎች የታጀበ እንደነበርም አውስተው፤ አሸባሪዉ ሕወሓት ከታሪካዊ ጠላቶቻችንና ከሌሎች ተላላኪ አሸባሪዎች ጋር በመተባበር ኢትዮጵያን ለማፍረስ ጦርነት የከፈተበት እና የአገር ሉዓላዊነትን በአደጋ ላይ የጣለበት ዓመት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በምዕራቡ የአገራችን አካባቢ የሕወሓት የሽብር ቡድን ፍልፍል የሆኑት ሸኔና ሌሎች አሸባሪ ቡድኖች ጠላቶቻችን ተልዕኮ በመቀበል ታሪክ የማይረሳቸውን ጥፋቶች በንፁሃን ዜጎቻችን ላይ መፈጸማቸውን፣ ንብረት ማውደማቸውና፣ ሕዝቡን ከቤት ንብረቱ ማፈናቀላቸውን ተናግረዋል፡፡

አሸባሪው ሸኔ የሚወግነው ብሄርም ሆነ ሰፈር ባይኖርም ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ለማባላትና ኢትዮጵያን የማያባራ የእርስ በርስ ግጭት ውስጥ ለማስገባት ብሔር ላይ ያተኮረ ጅምላ ግድያዎችን ፈጽሟል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የጥፋት ሃይሎቹ በሰው ሕይወት ላይ ከሚፈጽሙት ጥቃት በተጨማሪ ሀገር በምርት እጥረት ምክንያት የኮኖሚ ቀውስ ውስጥ እንድትገባ በማቀድ የመሰረተ ልማቶችን አውድመዋል፣ ፋብሪካዎችን የጥፋታቸው ኢላማ ማድረጋውን የዚሁ እየተጠናቀቀ ያለው ዓመት ፈተናዎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በሌላ በኩልም በ2014 ዓ.ም በምስራቁ የአገራችን ክፍልም አሸባሪው አልሻባብ የኃይማኖት ግጭንትን በመቀስቀስ የእርስ በርስ ግጭት እንዲፋፋም መሞከሩን አመልክተው፤ ቡድኑ ለ3ኛው የወያኔ ወረራ አስቀድሞ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት በማሰብ ከሸኔ ጋር በመቀናጀት ምስራቁን የአገራችን ክፍል የጦርነት ቀጠና ለማድረግ ጭምር ከፍተኛ ጥረት ያደረጉበት ዓመት እንደነበርም ጠቅሰዋል፡፡

በኢኮኖሚው ረገድም ፍላጎትና አቅርቦት ባለመጣጣማቸው፣ በየጊዜው በተፈጠሩ የኢኮኖሚ አሻጥሮች እንዲሁም በራሽያና ዩክሬን መካከል በተከፈተው ጦርነት ምክንያት ሕዝባችን በኑሮ ውድነት የተፈተነበት ዓመት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ባለፈው በጀት ዓመት ድርቅ ፤ ጦርነት እና የኑሮ ውድነት ፈተናዎች እንደነበሩ ያነሱ ሲሆን ፤ አሸባሪው ሕወሓት የከፈተው ጦርነት መቀልበሱን እና ሕዝብን ከብተና ማዳን መቻሉን የ2014 ስኬት መሆኑን አውስተዋል፡፡ እየተጠናቀቀ ያለው 2014 ዓ.ም ሕወሓት፣ አልሻባብ እና ሸኔን ጨምሮ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ኢትዮጵያን በከፍተኛ ደረጃ የፈተኑበት ዓመት ቢሆንም በብዙ ስኬቶች የታጀበም ዓመት ነበር ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፡-

እንዲሁም አልሸባብ የሽብር ቡድንን መከላከል መቻሉና ሽንፈትን ተከናንቦ ወደ መጣበት መመለስ መቻላችን ፤ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ተጠናክሮ መቀጠሉ፣ 3ኛው ዙር የውሃ ሙሌት በተሳካ ሁኔታ የተጠናቀቀበት እና ሁለተኛው ተርባይን ኃይል ማመንጨት መጀመሩ፣ ሀገሪቱ በምግብ እራሷን እንድትችል ተደረገውን ጥረት በዓመቱ የተከናወኑ ስኬቶች መሆናቸውን አንስተዋል፡፡

በተጨማሪም ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ያሉ ዜጎች ሕይወታቸው ለአደጋ እንዳይጋለጥ ሕይወት የማዳን ስራዎች መሰራታቸውንም አስረድተዋል።

ዓለምን ባስደመመው አራተኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር እንዲሁ 25 ሚሊዮን ችግኝ መትከል መቻሉ በ2014 ዓ.ም ከነበሩ ስኬቶች የሚጠቀሱ መሆኑን ነው ሚኒስትር ዴኤታው የገለጹት፡፡

የ2015 ዘመን መለወጫን ስንቀበል ለስኬት ያበቁንን ተሞክሮች እና እሴቶች በማጉላትና በመቀመር ለተጨማሪ ድሎች እንዲሁም አሁንም የተጋረጡብንን ፈተናዎች በድል ለመወጣት የሚያስችሉ መደላድሎችን በሚፈጥር መልኩ ነው ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሕጻናትን በጦርነት እየማገደ ያለው አሸባሪው ሕወሓት የትግራይ ሕዝብ መሰረታዊ ጠላት ነው!

ለትግራይ ሕዝብ ነጻነት እየታገልኩ ነው በሚል ሽፋን ከ50 ዓመታት በላይ መከራና ዕልቂት ሲዘራ የኖረው አሸባሪው ሕወሓት የሰላም አማራጮችን በመግፋት ሶስተኛ ዙር ጦርነት ከከፈተ አንድ ሳምንት ተቆጥሯል። በእነዚህ ቀናትም ሕጻናትንና ሴቶችን ለጦርነት በማሰለፍና ለዕልቂት በማመቻቸት አረመኔያዊ ባህሪውን ተገልጦ ወጥቷል።

አሸባሪ ቡድኑ ሕወሓት ጥንት በአንደኛው የዓለም ጦርነት ሥልጣኔና የዘመነ ጦር መሳሪያ ባልነበረበትና ጦርነትን በሰው ማዕበል ገጥሞ ማሸነፍ ብቸኛ አማራጭ በነበረበት ወቅት እንደሚደረገው ሁሉ ዛሬም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ከግብረ-ገብ፣ ከሞራልና ሕጋዊነት በእጅጉ በተጣረሰ አኳኋን በሰውነታቸው ያልጠነከሩ ሕፃናትን ለጦርነት አሰልፎ ታይቷል። በግፉ በለውም በሚገባ ሰልጥኖ እስከ አፍንጫው ከታጠቀ የመከላከያና ጥምር ኃይል ፊት እያሰለፈ የእሳት እራት አድርጎ በማስፈጀት የሥልጣን ዘመኑን ለማራዘም የዕውር ድንበር በመጓዝ ላይ ይገኛል።

ይህ አረመኔ ቡድን ገና በወላጅ አንክብካቤ ሊያድጉ፣ በትምህርት ገበታቸው ላይ ሊገኙ የሚገባቸውና ቦርቀው ያልጠገቡ ሕጻናትን በጦር አውድማ በማሰለፍ በለጋ ዕድሜያቸው ተቀጭተው እንዲቀሩ ለማድረግ ታትሮ እየሰራ ይገኛል። ይህን ታሪክ ይቅር የማይለውን ጭካኔ በገዛ ወገኑ ላይ የሚፈጽም አረመኔ ቡድን መሆኑን በዓለም አደባባይ እያስመሰከረ መጥቷል።

በሴራና ዘረፋ ተግባሩ የሚታወቀውና በጀግናው መከላከያ ሠራዊት ፊት የመቆም ወኔ የሌለው ይህ አሸባሪ ቡድን የሕዝብ ማዕበል የሚል ዘመኑ ያለፈበት የጦርነት ስልት በመከተል ሕጻናትንና ሴቶችን ጭዳ ለማድረግ ቆርጦ ተነስቷል። ለዚህም የአሸባሪ ቡድኑ መሪ የምናካሂደው ሕዝባዊ ጦርነት ነው ስለዚህ ሁሉም ይሳተፋል ሲሉ በአደባባይ መናገራቸው የሚታወስ ነው። 120 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት የመከላከያ ሠራዊት ግን የትግራይን ሕፃናት ከከንቱ እልቂት የመታደግ ሞራላዊና ሕጋዊ ግዴታ ስላለበት ሁኔታዎችን በዘዴና በስልት በማለፍና የተዘጋጀውን ወጥመድ በማምከን በድል አድራጊነት እየገሰገሰ ይገኛል።

የሽብር ቡድኑ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ተከፋይ፤ ጉዳይ አስፈፃሚና በወንጀል የሚፈለግ ሕገ-ወጥ ሽፍታ ቢሆንም መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ጥቅም በሚል የሰላም እጆችን በተደጋጋሚ ቢዘረጋም በአሸባሪ ቡድኑ ተነክሶ ተመልሷል። አሸባሪ ቡድኑ የአማራና የአፋር የተወሰኑ አካባቢዎችን ይዞ ባለበትና ለጦርነት እያንገራገረ በነበረበት ወቅት ሳይቀር መንግሥት ከ5ሺ600 በላይ የመኪና ጉዞ እና ከ270 በላይ በረራዎችን በማድረግ ወደ ትግራይ ምግብ፤ መድሃኒትና ነዳጅ እንዲገባ አድርጓል። ሆኖም ወደ ክልሉ የገባው ዕርዳታ የቡድኑ የዘረፋ ሲሳይ ከመሆን በዘለለ ለሕብረተሰቡ እንዳልደረሰ የሚያስረዱ ምስክሮች ተደምጠዋል። ለዘረፋና የዜጎችን ክብር ለማጉደፍ ላዘጋጀው በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ኃይል የሚያቀርበው ምግብም ከየትም የተገኘ ሳይሆን በትግራይ ሕዝብ ስም ከቀረበ እርዳታ መሆኑ ግልጽ ነው።

አሸባሪው ሕወሓት በዘረፋና በወንጀል የተጨማለቀ ታሪክ ያለው ቡድን ነው። በ1977 ዓ.ም የትግራይ ሕዝብ በርሃብ ሲጠቃ ከለጋሽ ሀገራት የተሰጠውን ስንዴ በመሸጥ ለጦር መሳርያ ግዥ አውሎታል። በዚህም ተግባሩ የትግራይ ሕዝብም በርሃብ ለመርገፍ በቅቷል። በዘረፋ ማንቱን የማቆየት አባዜ የተጠናወተው ይህ ቡድን ከዓለም የምግብ ድርጅት መጋዘን ውስጥ ከግማሽ ሚሊዮን ሊትር በላይ ነዳጅ በመዝረፍ ለወረራ ተጠቅሞበታል። የዓለም ምግብ ፕሮግራምም ሕወሓት የፈጸመውን ዘረፋ "አስደንጋጭ እና አሳፋሪ" በሚል የኮነነው ሲሆን ነዳጁ ካልተመለሰ በርካታ ዜጎች በርሃብ ሊሞቱ እንደሚችሉ ያለውን ስጋትም ገልጿል።

አሸባሪ ቡድኑ ቆሜለታለሁ ከሚለው ሕዝብ ጉሮሮ እየቀማ ጦርነት መለኮሱ ሳያንሰው በርሃብ አንጀቱ የሚሰቃየውን ሕዝብ በገፍ በማሰለፍ በጥይት አረር እንዲያልቅ አልሞ እየተጓዘ ይገኛል። ያለርህራሄ ሕጻናትን ፊት ለፊት አሰልፎ በአግባቡ ከሰለጠነና እስከ አፍንጫው ከታጠቀ ዘመናዊ ወታደር ፊት በማሰለፍም ከጭካኔዎች ሁሉ የከፋ ጭካኔን በትግራይ ሕዘብ ላይ እየፈጸመ ነው።

ስለሆነም ላለፉት 50 ዓመታት ያህል በትግራይ ህዝብ ጫንቃ ላይ እንደመዥገር ተጣብቆ የከፋት ፤የአረመኔነትና የጦርነት ምንጭ የሆነውን ይህን አሸባሪ ቡድን በማስገወገድ ሕጻናት በለጋ እድሜያቸው በጦርነት ከመርገፍ እንዲድኑ ሁሉም የሰው ዘር ሞራላዊ ግዴታውን ሊወጣ ይገባል!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ስለ ሰላም ሠርተንና ሕመማችንን ሽረን የምንቀራረብባትን አገር እንፍጠር

ብስለት

ዛሬ የከፋኝን ላወራ ልተነፍስ ነው ብዕሬን ከወረቀት ያገናኘሁት። በጣም ከፍቶኛል ውስጤ የገባውን ኀዘን ጮክ ብዬ አልናገር እሪ ብዬ አልቅሼ አይወጣልኝ ነገር ደረቴ ላይ እየተንቀዋለለ መተንፈሻ አሳጥቶኛል። የወገኔን እርም በልቻለው። የእኔ ሰው ሲያለቅስ አላለቀስኩለትም፤ ደረቱን ሲደቃ አብሬው ለሙሾ አለቆምኩም የእሱ እንባ እኔ ደጅ አልደረሰም በሬን አላንኳኳም ብዬ ይሁን፤ መንጋው ምን ይለኛል ምን ብዬ ከዚህም ከዛም ወገን የእናት የአባቴ ልጅ ሲረግፍ ጎረቤት ዘመድ አዝማዴ ድኳን ጥሎ ሲያነባ እኔ ግን እርሙን በልቼበታለሁ።

የአገሬ ሰው፥ ሰርግ ከቀረበት ሰው ይልቅ ለቅሶ የቀረበትን ነው የሚቀየመው። ሁሉም እኔን ተቀይሞኛል። ለቅሶውን ተበላልተናል። እርም አለብን። ባለአገር ማለት ለቅሶ ደራሽ ነው። እንባ አባሽ የእዝኑን ይዞ ሄዶ እንባ ማደረቂያ የሚያጎርስ ነው። ያለችውን ይዞ ለቅሶ ቤት አምሺ አዳሪው ነው። እኔ ግን ለዛ አልታደልኩም፤ እንደው በቁዘማ መሬቱን ስጭር አድራለሁ፤ ኀዘን ገፍቶ የደፋው አንገቴ የወገኔን ኀዘን መሸከም ያቃተው ጫንቃዬ በራሱ ነፍስ አውቆ አስጎንብሶኛል።

ውስጤ የሚንቀዋለለው ስሜት ወጥቶ ወይ ወርዶ ሰላም የምናገኘው ለቅሶ ስንዳረስ ነው። ምክንያቱም የጋራ ኀዘን ነው አገር የሚፈጥረው። የእገሊት ኀዘን እኔን ተሰምቶኝ የእሷ ኀዘን ውስጥ ገብቼ "ውይ በሞትኩ!" ስንል ነው አገር የሚፈጥረው። "አይ የእገሊት ቀብር ሰርግ ነበር የሚመስለው፤ እድለኛ ናት" የሚባለው ለኀዘንም ዕድል የሚያጠይቀው ኀዘን የጋራ ሆኖ አገር ስለሚሠራ ነው።

በምሽት፥ ለጎረቤት ጩኸት ሮጠን የምንሄደው ነገ እኛ ጋር ሮጠው እንደሚመጡ እርግጠኛ ስንሆን ነው። ከጀርባው ያለ ምልክት ይኼ ነው። ይኼን ባናስብ ተጠቅልለን ነበር የምተኛው። ጎረቤት ሲጮህ … "እነ እከሌ ቤት ችግር አለ" ብለን ያገኘውን ለብሰን አንዳንዱም ላዩ ላይ ብጣሽ ጥሎ እርቃኑን ሮጦ የሚሄደው ለዚህ ነው። ባለአገር መሆን ብድር ማቆየት ነው፤ ነግ በኔ ማለት። ባለአገር ማለት ቅኔው ከባድ ነው። በሰፈሩት ቁና የሚሰፈርበትን ቀን አስቦ የወገኔን በር ያንኳኳው ችግር፤ እገሌ ቤት የገባው ኀዘን እኔ ጋር ይገባል ብሎ አስቦ ነገ ለሚሆነው ዛሬ ተጠንቅቆ መኖር ነው።

ታዲያ የእኔን እርም ሳላወጣ የወገኔን ለቅሶ ሳልደርስ ለተበደለው ካሳ ሳይከፈል ለአዘነው የእዝን ሳይወሰድ ሳልስት አርባ ሙት ዓመት ሳይወጣ፤ ኀዘኑ የውስጥ ረመጥ አድርጎ ያዳፈነውን አንጀቱን እየለበለበ ያሳመመውን ህመም ሳስብ ነው አንገቴን የደፋሁ።

> **አገር ላይ ሰላም ለማስፈን፤ ጥላቻና ጦርነትን ለማቆም፤ ቂምና ቁርሾ እንዲሽር ማድረጊያ ዋናው መድኃኒት እርስ በእርስ መነጋገር ብቻ ሆኖ ሳለ፤ በባህላችንም ችግሮችን ለመፍታት የምንጠቀመው ሽምግልናን የመሰለ ወግ ከፊታችን ተቀምጦ፤ ምነው ጸብን በእርቅ ለመደምደም ከሽምግልና የበለጠ መፍትሄ አለመኖሩን ዘነጋን?**

እኔ እንኳን ኖርኩ ባልኩባት በዚህ ዕድሜዬ አገር ታማ ጣር ላይ በሆነችበት፤ የወገኔን እርም በበላሁበት ህመሙን ቁስሉን ማከም በተሳነኝ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ የአገሬ ህመሟ የወገኔ ኀዘኑ ነው ያስረጀኝ። የአገሬ ቁስሏ ነው ያቆሰለኝ። የበላሁት እርም ያላለቀስኩት ወገንን ፊት ማየት ተስኖኝ ነው ያጎነበስኩ።

ከሁሉ ከሁሉ የቆጨኝ ያቺ የሞተው ሞቶ የተረፉትን ለዘር ያድርግልኝ ብላ ልጆቿን በጉያዋ ወሽቃ የሰላም ንጋት ይመጣል እያለች ስትጠብቅ የነበረችትን እናት ተስፋ ማስቀጠል ያለመቻሌ ነገር፤ ደርሶ እየጠራ ያለውን የሰላም ውሃ ሲደፈርስ ተው ለማለት ያለመቻሌ ነገር፤ ዳግም በሰቀቀን ነጋ መሸ ነገ ምን ይመጣ ይሆን በሚል በሰለቸ ያፈጀ ሃሳብ ውስጥ ለመኖራቸው ከልካይ አለመሆኔ፤ በቃ ብዬ ሳልከላክልላቸው የመቅረቴ ነገር አንገቴን አስደፍቶኛል።

አገር ላይ ሰላም ለማስፈን፤ ጥላቻና ጦርነትን ለማቆም፤ ቂምና ቁርሾ እንዲሽር ማድረጊያ ዋናው መድኃኒት እርስ በእርስ መነጋገር ብቻ ሆኖ ሳለ፤ በባህላችንም ችግሮችን ለመፍታት የምንጠቀመው ሽምግልናን የመሰለ ወግ ከፊታችን ተቀምጦ፤ ምነው ጸብን በእርቅ ለመደምደም ከሽምግልና የበለጠ መፍትሄ አለመኖሩን ዘነጋን?።

ከሰዎች መካከል ተጽዕኖ ፈጣሪ፣ ታዋቂና አዋቂ ፣ተወዳጅ ፣ አንደበተ ርዕቱእ ፣ አስተዋይ ሰው ተመርጦ አንተም አንቺም ተው ባይ ሽማግሌ የሚሰየምበት ለሰፈር ለጎረቤት ብቻ ሳይሆን ለአገርም የሚያስፈልጋት ወግ ሽምግልና መሆኑን ስለምን ዘነጋነው እያልኩ እጠይቃለሁ።

ምነው በተለያዩ ጊዜያት ሽማግሌዎች ተልከው፤ የሰላም እናቶች የአገራችንን ሰንደቅ ዓላማ አንግበው በጡቶቻቸው ሲለምኑ፣ በእንባ እየተራጩ፣ በጉልበታቸው ጭምር ተንበርክከው ለሽምግልና አደባባይ ሲቆሙ አንገታችንን ሰበር ማድረግ የተሳነን? ምነው የሰው ጥላው፣ የሽማግሌ ግርማው አልከብድ አለን? ሌላው ቢቀር የሚላስ የሚቀመስ አጥተው በረሃብ እየረገፉ ያሉት ወገኖቻችን ጣር ለምን እኛ ፊት ላይ ምንም ርህራህ እንዳይፈጥር ሆነ?

ምነው ጥይት ከጨረሰው በላይ እኛው በፈጠርነው ችግር ምክንያት በበሽታ፣ የመድኃኒት እጦት፣ በረሃብ የሚጎሳቆልና የሚያልቀው ወገናችንን እርም በላን? ምነው በእኛ ጦረኝነት እንደ ቅጠል በሚረግፈው ወገናችን አስከሬን ላይ የሚፈጸም የመዘባበት ነውረኝነት መፀየፍ ተሳነን? ታዲያ ከዚህ በላይ ህመም፤ ከዚህ በላይ አንገት የሚያስደፋ ነገር ከየት ይመጣ ይሆን?

እኔ ግን ዕድሜዬን ረስቼ በእርጅና አቅም በማጣት እንድጠራወዝ አድርጎኛል። አገሬ ስለ ሰላም ሲል ጎንበስ የሚል፣ ስለ ሕዝቡ ሲል ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው የማጣቷ ነገር፤ አገሬ ጧሪ ደጋፊ ሳይኖራት የነገ ተስፋዋ ብሩሁን ቀን በልጆቿ እየጨለመ፤ ልጅ አልወጣላት ሲል ከመመለከት የተሻገረ ሌሎች አገሮች ከእኛ በሚፈሰው ወንዝ ልማት ሀብታቸውን ሲያሳድጉ እኛ በመነካከስ ላይ ቆመን፤ እርማችንን ስንበላላ የአንዱ ለቀሶ እኛን የማይገደን፣ የአንዱ ቁስል ሌላችንን የማያመን እንደ አገር ማሰብ ቀርቶ እንደ መንደር፤ እሱም ይቅር እንደ ቤተሰብ በሃሳብ መግባባት አቅቶን መደነቋቆርና መደነቋቆል የበዛበት ኑሮ አስልችቶኛል።

በጥቂቶች ፍላጎት ለሚያነባው ሕዝብ፣ በቡድኖች ቅዠት ለሚረግፈው ወገን፣ ለሰላም እንቢተኞች ሲባል ለሚጎሳቆለውና ነገው በአጭር እየተቋጨ ላለው ሕዝቤ ደርሼ እንባውን ያላበስኩለትም፣ ለቅሶውን ያላለቀስኩትም፣ በኀዘኑ ከጎኑ አልቆምኩለትም። እናም የዚህ ወገኔ ኀዘን አስጎንብሶኛል፤ ፊቱን ማየት አሰቅቆኛል። ለዚህም ነው "ይበቃል፣ ይበቃል፤…" ማለቴ። እናም በቃ ስለ ሰላም ሠርተንና ህመማችንን ሽረን የምንቀራረብባትን፤ አንዳችን ለአንዳችን አለኝታ የምንሆንባትን አገር እንፍጠር።

Website - www.press.et Email - addiszemen@press.et Facebook - Ethiopian Press Agency

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

# ተጠየቅ

## ‹‹የምርት እጥረት የለም፤ በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ግን ልዩነት አለ››

**ወይዘሮ ሰርካለም ጌታቸው**
**የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር**

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን መልከ ብዙ ገፅታዎች የተላበሰ ነው። ዘመናትን በተሻገረው አገልግሎቱ ሙገሳም ወቀሳም እያስተናገደ ይገኛል። በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የአዲስ አበቤ ነዋሪዎች ጥያቄ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሆኗል። ወዲህ ደግሞ ባለስልጣኑ የነዋሪዎችን ጥያቄ ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ስለመሆኑ ማስረጃዎችን ጭምር በማቅረብ ኃላፊነቱን እየተወጣ ስለመሆኑ ይናገራል።

ለአብነት እንኳን በ2014 በጀት ዓመት የለገዳዲ ክፍል ሁለት የከርሰ ምድር ውሃ ፕሮጀክትን በማጠናቀቅ 860ሺ የከተማዋን ነዋሪዎች የንጹህ ውሃ ተጠቃሚ የሚያደርገው ሥራ ማከናወኑን አስታውቋል። ለዚህም አራት ቢሊዮን ብር በጀት የተበጀተለት እንደነበርና ከሁለት እስከ አምስት ሺህ ሜትር ኪዩብ ውሃን በየቀኑ መያዝ የሚችሉ የውሃ ጉድጓዶች ግንባታ የፕሮጀክቱ አካል ነበሩ ሲል ጥረት ማድረጉን አጋርቶናል። ይህ ለአብነት ይጠቀስ እንጂ ባለስልጣኑ እጅግ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ፈሰስ በማድረግ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን ላይ መሆኑንም ያብራራል።

የባለስልጣኑን የኋልዮሽ ታሪክ እንደሚጠቁመው፤ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የቧንቧ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑት በ1893 ዓ.ም ነበር። ይህም የአፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥት የውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ በሆነ ሰባት ዓመታት ዘግይቶ ነበር። የቧንቧ ውሃ አገልገሎት መጀመርን ተከትሎ አገልግሎቱን ማን ይስጠው የሚለውን መልስ መሻትም ግድ ነበር። በመጀመሪያ የሥራ ሚኒስቴር በመባል ይታወቅ የነበረው መስሪያ ቤት ይህን ኃላፊነት ሲወጣ ቆይቶ ከጣሊያን ወረራ በኋላ በ1934 ዓ.ም የከተማዋ ማዘጋጃ ቤት እንደገና ሲዋቀር ደግሞ ‹‹የውሃ ማደረጃ ዋና መስሪያ ቤት›› በሚል ስያሜ እንደ አንድ የሥራ ክፍል የውሃ አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል ተቋቋመ። እነዚህን ሂደቶች አልፎ በአሁኑ ወቅት የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የሚል ስያሜ አግኝቷል።

ይህ ተቋም በአሁኑ ወቅት ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች ከምድርና ገፀ ምድር ውሃ በማፈላለግና በማልማት ውሃ እያቀረበ ነው። በዚህም በቀን ከ700ሺ ሜትር ኪዩብ በላይ ውሃ እያቀረበ ነው። ይሁንና የከተማዋ ዕለታዊ የውሃ ፍጆታ 1ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ገደማ ነው።

ለከተማው ነዋሪዎች የገፈርሣ ግድብና ማጣሪያ ጣቢያ፣ የለገዳዲ ግድብና ማጣሪያ ጣቢያ እንዲሁም የድሬ ግድብ ከፍተኛ ውሃ የማምረት አቅም ያላቸው ሲሆን፤ ሌሎች ጉድጓዶችና የከርሠ ምድር ምንጮች ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው። ባለስልጣኑ ከእነዚህ በተጨማሪ ሌሎችንም እያለማ የኅብረተሰቡን ጥያቄ ለመመለስ ደፋ ቀና እያለ ስለመሆኑ ይነገራል።

በዛሬው ዕትማችን ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰርካለም ጌታቸው ጋር የባለስልጣኑን የአገልግሎት አሰጣጥና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ቆይታ አድርገናል።

**አዲስ ዘመን፡- በ2014 በጀት ዓመት ዓበይት ክንውኖች ምንድን ናቸው?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን የኦፐሬሽን፣ ጥገና እንዲሁም አዳዲስ ፕሮጀክቶችን በየዓመቱ እያቀደ ይሠራል። በበጀት ዓመቱም በዋናነት ካሉ ግድቦች ጉድጓዶች ውሃ አሰራጭቶ በማምረት ረገድ 188 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ አምርቶ ለተጠቃሚዎች አሰራጭቷል። ይህም ከዕቅዱ 86 ከመቶውን ይሸፍናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስምን 86 ከመቶ ብቻ ሆነ?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** 86 በመቶ ብቻ የሆነው የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ፣ የጉድጓድ ውሃ መጠን መቀነስና የመሳሰሉት ለምርቱ መቀነስ በዋናነት የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው። ነገር ግን ከሁሉም ምክንያት እንደባለስልጣኑ ከፍ ብሎ ያየነው የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ነው። ከ220 በላይ ጉድጓዶች፣ ሦስት ግድቦች እና ሁለት ማጣሪያ ጣቢያዎች አሉን። ሆኖም በእነዚህ ሁሉ ላይ ጀኔሬተር አናስቀምጥም። ሆኖም በጣም ትልልቅ የሆኑ 87 ዲዝል ጀኔሬተሮች አሉን። በእነዚህ ጀኔሬተሮች ብቻ በ2014 በጀት ዓመት 870 ሺህ ሊትር ነዳጅ ተጠቅመናል። ይህ የኤሌክትሪክ መቆራረጠን ለመቋቋም የተደረገ ጥረት ነው። ባለፈው ዓመት ከነበረው ተመሳሳይ ወቅት አኳያ ሲታይ 220 ሊትር ብልጫ አለው። ይህ የሚያሳየው በበጀት ዓመቱ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ከ2013 በጀት ዓመት አኳያ ከፍ ያለ መሆኑን ነው።

በፍሳሽ በኩል 38 ሚሊዮን 457ሺ 440 ሜትር ኪዩብ ፍሳሽ አሰባስበንና አጣርተን አስወግደናል። 73ሺ የቤት ለቤት የዘመናዊ ፍሳሽ ቅጥያ ሥራ አከናውነናል። ይህም በዘመናዊ መንገድ ፍሳሽ በማሰባሰብ አጣርቶ ማስወገድ ሽፋን ከ31 ከመቶ ወደ 34 ከመቶ አሳድገናል። ይህም ማለት አብዛኛዎቹ በዘመናዊ መንገድ ወይንም በመስመር ፍሳሽ ማስወገድ ማለት ነው። 38 ትልልቅ ማጣሪያዎች አሉን።

ጎን ለጎን የውሃ አቅርቦት ችግርን ለማቃለል የለገዳዲ ቁጥር ሁለት የውሃ ፕሮጀክትን አጠናቆ ለአገልግሎት ማብቃት ዋነኛ ዕቅድ የነበረ ነው። ይህ ፕሮጀክት 16 ጥልቅ ጉድጓዶች፣ 10 የውሃ ማጣሪያ ጋኖች እያንዳንዳቸው ከሁለት ሺህ እስከ አምስት ሺህ ሜትር ኪዩብ ውሃን መያዝ የሚችሉ ናቸው። 180 ኪሎ ሜትር የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ 38 ኪሎ ሜትር የመዳረሻ መንገድ ግንባታ እና ሁለት ግዙፍ ግፊት መስጫ ጣቢያዎችና ኤሌክትሮ መካኒካል በውስጡ የያዘ ነው። በቀን 86ሺ ሜትር ኪዩብ መስጠት የሚችልና 860ሺ የከተማዋን ነዋሪዎች የንጹህ ውሃ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው። ይህ ፕሮጀክት ታሳቢ ተደርጎ የተሠራው የጉለሌ እና የየካ ክፍለ ከተሞች ተራራማ አካባቢ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በነዋሪዎች ከፍተኛ የውሃ እጥረት እንዳለ ይገለፃል። ይህ ለምን ሆነ?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** በዋናነት በበጀት ዓመቱ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ተቋቁሞ 644ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃ አምርቶ ለማሰራጨት ነው እቅዱ። ከእቅዱ ትልቁን ማሳካት ተችሏል። የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ይፋ ያደረገው ባይሆንም የአዲስ አበባ ሕዝብ ብዛት 4ነጥብ2 ሚሊዮን ነው ብለን ብናስብ፤ በቀን የሚያስፈልገው ውሃ 1ነጥብ2 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ነው። ስለዚህ ያለን አቅምና ኅብረተሰቡ የሚፈልገው የውሃ ፍላጎት መካከል ልዩነት አለ። ስለዚህ ውሃውን በፍትሃዊነት ለማዳረስ ስንል የፈረቃ መርሐ ግብር እንከተላለን።

በዋናነት የከተማችን ሕዝብ እንዲገነዘብ የምንፈልገው ነገር አለ። የመጀመሪያው ከተማዋ የአፍሪካ መዲና እና የኤምባሲዎች መቀመጫ ናት። አየር መንገዳችንም ትልቁ ምስላችንና መለያችን ነው። የሚፈልጉት ውሃም ከፍተኛ መሆኑን ታሳቢ ማድረግ ተገቢ ነው። መሠረታዊ አገልግሎት የሚሰጡ የፌዴራል ተቋማት፣ ሆስፒታሎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ባለኮከብ ሆቴሎችና የመሳሰሉት ከፍተኛ የውሃ ፍላጎት አላቸው። የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ፣ የከተማ አረንጓዴ ልማት፣ ሰፋፊ መሠረተ ልማቶችም፣ የምናመርተውን ውሃ ይፈልጋሉ። ስለዚህ የፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ችግር ወደ ፈረቃ እንድንገባ አድርጎናል።

ነገር ግን በእኛ ግምገማ ትልቁን ጩኸት የሚያነሱት ኢ-መደበኛ ነዋሪዎች በተለይም የማስፋፊያ አካባቢ ያሉ ክፍለ ከተሞች፣ መንግሥት ለአረንጓዴ ልማትና ለመሳሰሉት ያስቀመጣቸውን ቦታዎችን ኢ-መደበኛ በሆነ ሁኔታ የተያዙ ቦታዎች ይህን ጥያቄን በተደጋጋሚ ያነሳሉ። አሁን ባለን አሠራር በመሰል አካባቢዎች የውሃ መስመር የለንም፤ ውሃ ለማቅረብና መስመሩን ለመዘርጋትም ነዋሪዎች ካርታ እና ፕላን ሊኖራቸው ይገባል። እንደ ዜጋ ደግሞ ውሃ ማግኘት አለባቸው። በመሆኑም በእነዚህ አካባቢዎች የውሃ ሮቶ አስቀምጠንና በትልቅ ተሽከርካሪዎች ውሃ አመላልሰን እየሞላን ውሃ እንዲያገኙ እያደረግን ነው። ሌሎች ቦታዎች ግን መስመር ያላቸውና በሳምንት የሚያገኙት ምክንያቱ ከምንጬ የውሃ እጥረት ሲከሰት እና መብራት ሲጠፋ ፈረቃው ይዛባል። በመሰል አጋጣሚዎች በሳምንት አንድ ቀን ውሃ ሲያገኙ የነበሩት በሁለት ሳምንት የሚያገኙበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። ይህ ሲሆን ግን እኛ የምናደርገው በተሽከርካሪ ውሃ ማቅረብ ነው። አልፎ አልፎ ደግሞ መስመር ሊበላሽ ይችላል። በዋናነት የምናደርገው ግን ሰዎች ፈረቃቸውን እንዲያውቁ ነው። ቴክኒካል ችግሮች ሲገጥሙን ደግሞ በተቻለ ፍጥነት ለማስተካከል እንሞክራለን።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ባለው ሁኔታ አቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠኑን ገልፀውልኛል። ስለዚህ የውሃ ምርት አቅርቦት ችግር አለ ማለት ነው?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** የውሃ ምርት እጥረት የለብንም። ምርት ማለት ባለ አቅም ማለትም ባሉ ጉድጓዶች እና የከርሰ ምድር የሚመረት ውሃ ማለት ነው። 220 ጉድጓች አሉን። ከገፀ ምድርም ለገዳዲ፤ ገፈርሳ ውሃ እናገኛለን። ለዚህም በቂ ኬሚካል አለን፤ ብዙ ጊዜም እጥረት አጋጥሞን አያውቅም። በመሆኑም ውሃም አክመን እናቀርባለን። ብዙ ጊዜም ኬሚካሉን ቀደም ብለን ገዝተን እንይዛለን። ስለዚህ ባሉን መሠረተ ልማቶች ውሃ እየተመረተ ነው። ነገር ግን ‹‹መሠረተ ልማቶቹ የሚያመርቱት ውሃ እና ከተማዋ የምትፈልገው ውሃ አይጣጣምም›› የሚለው ዋናው ሃሳብ ነው። ከተማዋ በቀን አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ትፈልጋለች። የእኛ 644 ሺ ሜትር ኪዩብ ነው። አዲስ የተመረተውን የለገዳዲን 86ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃ ስንጨምርበት 730 ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃ



**የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ይፋ ያደረገው ባይሆንም የአዲስ አበባ ሕዝብ ብዛት 4ነጥብ2 ሚሊዮን ነው ብለን ብናስብ፤ በቀን የሚያስፈልገው ውሃ 1ነጥብ2 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ነው። ስለዚህ ያለን አቅምና ኅብረተሰቡ የሚፈልገው የውሃ ፍላጎት መካከል ልዩነት አለ**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

ነው የሚሆነው። ስለዚህ አልተጣጣመም።

**አዲስ ዘመን፡- አቅርቦትና ፍላጎት አልተጣጣመም ማለት፤ የምርት እጥረት አለ ማለት አይደለምን?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** አይደለም! የምርት እጥረት ሳይሆን የአቅርቦት እጥረት አለ። ምርት ማለት የሆነ ፋብሪካ የማምረት አቅም ኖሮት፤ ፋብሪካው ሙሉ ለሙሉ አለማምረት ነው። ለምሳሌ 100ሺ ማምረት እየቻለ 50ሺ ካመረተ የምርት እጥረት አለ ይባላል። ምክንያቱም የማምረት አቅሙ 100ሺ ስለሆነ። በእኛ አግባብ ግን ያለማናቸው ጉድጓዶች ማምረት የሚችሉትን እያመረቱ ነው። ፍላጎቱ ግን ከዚህ በላይ ከፍ ያለ ነው። ሌሎች የውሃ ፕሮጀክቶች መጀመርና መከናወን አለባቸው። በእኛ አነጋገር የምርት እጥረት የለም፤ ግን በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ልዩነት አለ። እኛ የምረዳው፤ የምርት እጥረት ማለት ባለ አቅም አለማምረት ማለት ነው። እኛ ባለን አቅም እያመረትን ነው። አንተ የምትረዳው የምርት እጥረትና እኛ የምንረዳው የምርት እጥረት የተለያየ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኅብረተሰቡ በመስመር ድፍርስ ውሃ እያጋጠመን ነው። ይህ ከዓለም አቀፍ ነባራዊ ሁኔታም አኳያ የኬሚካል እጥረት ሳይኖር አይቀርም ይላሉ። እርስዎ ከላይ በገለፁት ሀሣብ መሠረት ኅብረተሰቡ ተሳስቶ ይሆን?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** አዎ ስህተት ነው። በዋናነት ኬሚካል የሚፈልጉት ለገዳዲ፣ ገፈርሳ የመሳሰሉት ከገፀ ምድር የውሃ ምርት የሚሰጡን ናቸው። ለዚህ የሚሆን ኬሚካል እጥረት አጋጥሞን አያውቅም። ኬሚካል በበቂ ሁኔታ አለ። የዓለም የጤና ድርጅት የሚያስቀምጠውን መስፈርት በሚያሟላ ደረጃ አክመን ነው የምንለቀው። ነገር ግን አልፎ አልፎ የመስመር ብልሽት ሲያጋጥም በቅጽበት በቁጥጥር ስር የሚውል አይደለም። ጥቆማ ደርሶንና ባለሙያ ደርሶ እስከሚዘጋው ድረስ ውሃ በፍጥነት ግለሰቦች ቤት ሊደርስ ይችላል። ይሁንና መሰል ችግሮች ሲጋጥሙን ወዲያውኑ ዘግተን፤ መስመር ውስጥ ያለውን ውሃ ደግሞ ደፍተንና መስመሩን ጠግነን ንፁህ ውሃ ለተጠቃሚ እናደርሳለን። ከዚህም በተጨማሪ በየቀኑ 30 የሚሆኑ ናሙናዎችን እንወስዳለን። ይህም ከጉድጓዶች፣ ከግለሰቦች፣ ከማጠራቀሚያ ጣቢያዎች ናሙና ወስደን እንፈትሻለን።

ውሃው የዓለም ጤና ድርጅት መስፈርትን ስለማሟላቱ፤ ጤናማ ስለመሆኑ ተጣርቶ ነው የሚሰራጨው። ነገር ግን ግለሰቦች አንዳንድ ነገሮችን ሲከውኑ ጭምር መስመር ይሰብሩና ባዕድ ነገር ከውሃው ሊቀላቀል ይችላል። ከዚህ በኋላ ቅሬታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። አልፎ አልፎ ደግሞ ጎርፍ ጉድጓድ ውስጥ ሊገባ ይችላል። ሆኖም በቅጽበት እናፀዳዋለን። ውሃ ማምረት እንደ ምግብ ፋብሪካ ነው። በመሆኑም ደረጃው ያልጠበቀውን ውሃ ለመልቀቅም ለማሰራጨትም አዋጁ አይፈቅድልንም፤ እኛም የምንጠቀመው ውሃ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ባለስልጣኑ የሚያከናውናቸው አንዳንድ ፕሮጀክቶች ይፈጥናሉ፤ አንዳንዶች ለዓመታት ይዘገያሉ። ይህ ከምን የተነሳ ነው ?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** የተጓቱት የት ናቸው? እኛ ዘንድ ወይስ ሌላ ቦታ? በእርግጥ ይህ ዘገየ ብለህ ጠርተህ ያቀረብክልኝ ነገር የለም።

**አዲስ ዘመን፡- እናንተ ዘንድ የተጓተቱ ፕሮጀክቶች የሉም ማለት ነው?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** ምን መሰለህ፤ የውሃ ፕሮጀክቶች ከሌሎች በዋናነት የሚለየው የሚጠቀማቸው ግብዓቶች «ሸልፍድ» ቀድሞ ተገዝቶ የሚቀመጥ አይደሉም። ለምሳሌ አንድ ግንባታ ለማከናወን ሲፈለግ ሲሚንቶ፣ ብረት፣ ቆርቆሮ የመሳሰሉትን ሄዶ ገዝቶ መጠቀም ይቻላል። የውሃ ፕሮጀክት ግን እንደዚያ አይደለም። የለገዳዲ ውሃ ፕሮጀክት እጥረት ስላለ እና በጣም በከፍተኛ ክትትል የተሠራ ነው። የውሃ ፕሮጀክት ትልቅ ኢንቨስትመንት ይጠይቃል። ማስተዋል ያለብን ነገር ቢኖር፤ መንግሥት ሁሉን በጀት ለውሃ በጅቶ ሌሎች ፕሮጀክቶችን መተው አይችልም።

ሁለተኛው ደግሞ አብዛኞቹ የውጭ ምንዛሪ የሚፈልጉ ናቸው። የውሃ ፕሮጀክቶች ጨረታው ወጥቶ ከዚያም ጨረታው ያሸነፈው አካል ተለይቶ ኤል.ሲ ‹ሌተር ኦፍ ክሬዲት) ሊከፈትለት ይገባል። ‹ሌተር ኦፍ ክሬዲት) ከተከፈተ በኋላ በዓለም ላይ ለአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ተብሎ ነው የሚመረተው። ምክንያቱም እዚህ የጥራትና ዲዛይን ሥራ ተሠርቶ በሚፈለገው ዲያሜትርና ስፋት ነው የሚታዘዘው። ይህም ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት ይወስዳል። ምርቱ ተመርቶ አገር ውስጥ እስከሚገባ ድረስ፤ ከተመረተ በኋላም ረጅም ጊዜ ይወስዳል። ስለዚህ የውሃ ምርት ከሌሎች የሚለይበት አንዱ ይህ ነው። የውሃ ኢንቨስተመንት ውድ በመሆኑም በየጊዜው አዳዲስ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደ ሥራ እንዳይገቡ ያደርጋል። ጥቅም ላይ የሚውሉ አብዛኞቹ ግብዓቶችም በትዕዛዝ ተመርተው ወደ አገር የሚገቡ መሆናቸው ነው። አንዳንድ ፕሮጀክቶች ከመንግሥትም አቅም በላይ የሚሆኑ፤ የፋይናንስ አማራጭ የሚፈለግላቸውና ብድር የሚፈለግላቸው ይኖራሉ። በመሆኑም አበዳሪዎች ብድሩን እስከሚፈቅዱ ድረስ መጠበቅ ትልልቅ ፕሮጀክቶች እንዲዘገዩ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳሉ።

> **ውሃው የዓለም ጤና ድርጅት መስፈርትን ስለማሟላቱ፤ ጤናማ ስለመሆኑ ተጣርቶ ነው የሚሰራጨው። ነገር ግን ግለሰቦች አንዳንድ ነገሮችን ሲከውኑ ጭምር መስመር ይሰብሩና ባዕድ ነገር ከውሃው ሊቀላቀል ይችላል**

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህን ችግሮች ከግምት ውስጥ አስገብቶ ስትራቴጂክ እቅድ ማቀድና ቀድሞ የሚጠበቅበትን ማከናወን የባለስልጣኑ ሥራ አይደለም እንዴ?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** ይህን ባለስልጣኑ እንዳላደረገ አንተ እርግጠኛ መሆን ትችላለህ?

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ እየጠየኩኝ ያለሁት በዚህ ላይ እርግጠኛ ለመሆንና፤ ኅብረተሰቡም መረጃውን እንዲያውቅ መሆኑ አልተረዱም?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** በጣም ጥሩ ነው። ለማንኛውም «ዩቲሊቲ» በአደጉ አገራት የአምስት ዓመት እና አስር ዓመት አይያዝም። የ50 ዓመትም፤ የ100 ዓመትም ይይዛሉ፤ እኛ ድህነታችን ነው። እኛ እንደ ተቋም ጥናት ያካሄድንባቸው አሉ። ስትራቴጂክ ሆኖ መሄድ ይገባል ላልከው፤ እጃችን ላይ ሦስት ትልልቅ የውሃ ፕሮጀክቶች አሉን። ከአገር አቅም ጋር ነው የምንሄደው። ለጥናት ሞልቶናል። እጃችን ላይ ገርቢ አለ ካጠናነውም ቆይቷል፤ ጥሩ እየሄደ ነው። አለልቱ ሲዳ-ሮቢ የሚባል አለ፤ ይህም ትልቅ ፕሮጀክት ነው። የወሰን ማስከበር ሥራዎችን እየሠራን ነው። እነዚህን ሁሉ አጥንተን የተጠናቀቁ፤ ጥናታቸውም በዚህ አመት የሚጠናቀቅ አለ።

እነዚህ ትልልቅ የውሃ ፕሮጀክቶች ናቸው። ስለዚህ ‹ስትራቴጂካሊ› መንግሥትም እኛም ቀድመን አቅደን፣ አስጠንተን፣ ዲዛይኑን አጠናቀን ይዘን ፋይናንስ እየተፈለገላቸው የሚገኙም አሉ። ከውጭ አበዳሪዎቹ ለፕሮጀክቶቹ እንዲያበድሩን ፋይናንስ እያፈላለግን ያሉ ፕሮጀክቶች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- የውሃ መስመር ሲባለሸና ለአንዳንድ አገልግሎቶች ባለሙያዎች በአግባቡ አያገለግሉም፤ ገንዘብ ይጠይቃሉ የሚሉና ሌሎች የሥነ-ምግባር ጥሰት ይነሳል። ባለስልጣኑ ምን ይላል?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** ባለሙያዎች ሳንቲም መጠየቅና ሌሎች ነገሮችን በተመለከተ እኛ ዘንድ ከወሬ ባለፈ የደረሰን ምንም ተጨባጭ ማስረጃ የለም። ይሁንና በወሬ ደረጃ እንሰማለን። ሆኖም ኮሚቴም አዋቅረን እስከታች ድረስ ወርደን ለማጣራት ስንሞክር ምንም ይህ ነው የሚለን የለም። በዚህ አጋጣሚ ለኅብረተሰቡ ማሳወቅ የምንፈልገው ነገር መሰል ድርጊቶችን ከተመለከቱ በአስቸኳይ ካሳወቁን ለእኛ በቂ ነው። እኛ እንደዚህ ዓይነት ባለሙያዎች ካሉ የምንታገስበት ጫንቃ የለንም። በውሃ እጥረት ላይ የሥነ ምግባር ጉደለት ፈጽሞ አይመከርም። በጣም ከፍተኛ ፍተሻ እናደርጋለን፡ ነገር ግን በተጨባጭ አላገኘንም። አንዳንዴ ባለሙያዎች ፈረቃ ለመስራት ሲሄዱ ውሃ ሌላ አካባቢ ለማሰራጨት የሚመስላቸው አሉ። ሌላው በየመንደሩ «ፎካል ፐርሰን» አለን። ውሃ በአግባቡ ስለመድረሱና ቴክኒሺያን በአግባቡ ስለመሥራታቸውም ግምገማ ይደረጋል።

**አዲስ ዘመን፡- የ2015 በጀት ዓመት አንኳር እቅዶች ምንድን ናቸው?**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** ባለስልጣኑ በ2015 በጀት ዓመት በርካታ ተግባራትን የሚያከናውን ሲሆን የኅብረተሰቡን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ያደርጋል። በበጀት ዓመቱም የትኩረት አቅጣጫዎችም ተለይተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የከተማዋን የውሃ አቅርቦትና ፍላጎት ክፍተትን ሊቀንሱ የሚችሉ የተጀመሩ የውሃ ልማት ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል እንዲሁም በወቅቱ እንዲጠናቀቁ ማድረግ፣ የከተማዋን ፍሳሽ አገልግሎት ሊያሳድጉ የሚችሉ የተጀመሩ የፍሳሽ ልማት ሥራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሳኒቴሽን ተጠቃሚ ማድረግ፣ ተቋማዊ የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም ሥራዎችን ተግባራዊ ማድረግ፣ ለአዲስ አበባ የውሃ መገኛ የሆኑ የኦሮሚያ አካባቢዎችን የጋራ ተጠቃሚነትን ባረጋገጠ መልኩ የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው።

የውሃ ዕጥረት በሚታይባቸው የከተማዋ ኪስ ቦታዎች የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ በማከናወን እና በቀን እስከ 40 ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃ በማምረት ከ400 ሺ በላይ ለሚደርሱ የከተማዋ ነዋሪዎች የንጹህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ በበጀት ዓመቱ መቶ ፐርሰንት እንዲደረስ ይደረጋል። ከ2014 በጀት ዓመት የዞሩ ከስድስት ጉድጓዶች ቁፋሮ ውስጥ የቀሪ አምስት ጉድጓዶች ቁፋሮ ሥራ መቶ በመቶ ማጠናቀቅ፣ የአማካሪ ቅጥር በመፈፀም ለጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ የጥናትና ሱፐርቪዥን ሥራውን መቶ በመቶ ማጠናቀቅ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው።

የተቋራጭ ቅጥር በመፈፀምም የ15 የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ (በተለያዩ ሎቶች) ሥራ ማከናወን፣ የተቋራጭ ቅጥር በመፈጸም የ31 ጉድጓዶች የፓምፕ አቅርቦትና ተከላ ሥራ ማከናወን፣ ለትራንስፎርመር አቅርቦት፣ ለመብራት ኃይል እና የትራንስፎርመር ተከላ ሥራ በመብራት ኃይል በኩል መቶ ፐርሰንት ክፍያ መፈጸም፣ የተቋራጭ ቅጥር በመፈጸም የአምስት ጉድጓዶች የመስመር ዝርጋታ እና ከሪዘርቫየር ጋር የማገናኘት ሥራ ማከናወን፣ የመስመር ዝርጋታ እና ተያያዥ የሲቪል ሥራዎች ማከናወንም ግብ ተደርገው የሚሠሩ ናቸው።

በበጀት ዓመቱ በኮዬ ፈጬ አካባቢ ከዚህ ቀደም የተቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶች በተለያዩ ምክንያቶች የቀነሰው የውሃ ምርት የመስጠት አቅምን ለመመለስ እና በዘላቂነት አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ተግባራዊ በመደረግ ላይ ያለው በቀን 35 ሺ ሜትር ኩብ ውሃ እንደሚሰጥ የሚጠበቀው ፕሮጀክት አሁን ካለበት 17 ከመቶ ወደ መቶ ፐርሰንት እንዲደርስ በትኩረት ይሠራል። ለትራንስፎርመር አቅርቦት አስፈላጊው ክፍያ ለመብራት ኃይል እና የትራንስፎርመር ተከላ ሥራ በመብራት ኃይል በኩል መቶ በመቶ ክፍያ መፈጸም፣ የዲዛይን፣ የመስመር ዝርጋታ እና ተያያዥ የሲቪል ሥራዎች በማከናወን በቀን እንዲሁም 35 ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃ ወደ ሥርጭት ማስገባት ዋነኛ የትኩረት መስኮች ሲሆኑ፤ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 75ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃ ወደ ስርጭት ማስገባት ታሳቢ በማድረግ ባለስልጣኑ በትጋት የሚሠራ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡኝ መረጃ በዝግጅት ክፍላችን ሥም አመሰግናለሁ።**

**ወይዘሮ ሰርካለም፡-** አመሰግናለሁ። ጥቅሙ የጋራ በመሆኑ በጋራ እንሠራለን።



ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ስለ ልጆቻችን እንዘምር ወይንስ እንቆዝም!?

ስለ ልጆቹ በጎ በጎውን ብቻ ካልሆነ በስተቀር ጥፋታቸውንና ድክመታቸውን ለማድመጥ የበርካታ ኢትዮጵያዊያን ወላጆች ጆሮ እጅግም የተከፈተ አይመስልም። “የእኔ ልጅ እኮ…!” እየተባለ አዘውትሮ በወላጆች የሚዘመረው ብቃታቸውና የባህርያቸው ውብትና ድምቀት ነው። ስህተታቸው ይፋ እንዲገለጥና የተገለጠው ስህተትም ሥር ሳይሰድ በባለሙያዎች እገዛና በወዳጆች ምክር እንዲታረም የመፈለጉ መነሳሳት በብዙዎች ዘንድ እጅግም ተመራጭ አይመስልም።

የዚህን መሰሉ ማሕበራዊ ህፀፃችን ዋነኛ ሰበብና ምክንያቱ ለብዙ ምርምር የሚጋብዝ ሳይሆን ያሳደገን ማሕበረሰብ እንዲህ ሆነን ሕይወትን እንድንመራ ቀርጾ ስለሠራን ነው። እንዴታውን እናብራራ፡- “ኑሮና መቃብር ለየብቻ ነው” በሚለው ነባር ባህል ተጠፈንጎ በኖረ ማኅበረሰብ ውስጥ የተፈጠረው የዛሬው ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ “የልጆቹን የችግር ገመና” ገላልጦ ለመፍትሔው ከመድከም ይልቅ፤ “በሩን ዘግቶ ተከድኖ ቢበስል” መምረጡ የኖርንበትና የተለማመድነው “ጥብቅ ኩራታች” ሆኖ እንደተጣበቀን እነሆ ዘመናትን ለመሻገር በቅቷል።

“እህል ከሆነ ይጠፋል፤ ልጅ ከሆነ ይገፋል” ተብሎ እንደተተረተባት እርጉዝ ሴት፤ ዛሬ ዛሬ የሆነውን እንዳልሆነ በመቁጠር “ልጄ/ልጆቼ እኮ…!” እያልን በይሉኝታ ስናሽሞነሙን የኖርነው ችግራችን ከዕለት ወደ እለት ከመቀነስ ይልቅ እየባሰና እየተወሳሰበ ሄዶ ፍሬው ተንዠርግጎ በመገለጡ በአንክርዳድ የተጠመቀውን “ጉሽ” እንደ ማሕበረሰብ እየመረረንም ቢሆን ለመጎጨት ግድ ብሎናል። ይህን መሰሉን የቤታችንን የፈተና ቋጥኝ እንደ ወላጅ በግልጽ እየተወያየን፣ እንደ ሀገር ቅድሚያ ሰጥተን እየመከርን ወደ መፍትሔው መቃረብ እስካልቻልን ድረስ ልጆቻችን በወላጆቻቸው ቤት ውስጥ እየኖሩ ባእዳን ባለሀገሮች ወደ መሆን ደረጃ እንዳይሸጋገሩ ስጋቱ አስፈሪ ብቻ ሳይሆን ሀገራዊ ችግሩም በቀላሉ ላይቀለበስ ይችላል።

ይህ የጋራ “ቁስላችን” ማስረጃና ማረጋገጫ የሚያስፈልገው አይደለም። “በቀይ መብራት” ጭምር እያስጠነቀቀንና እየቀሰቀሰን እንድንነቃ የሚጎተጉተንን የየቤታችንን የልጅ አስተዳደግና የአስተዳደር ተሞክሮን ብቻ መመልከቱ በቂና ከበቂ በላይ ይሆናል። ለአደጋው ክብደት ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ በግልጽነት ከመወያየት ይልቅ ዛሬም ከጋራ ችግሮቻችን ዐይን አፋርነት ለመላቀቅ ጥረት ያለማድረጋችን ሊታሰብበት ይገባ ይመስለናል። አንዳንዶቹን መሠረታዊ ምክንያቶችና ውጤታቸውን ከታሪክም ከነባራዊ ሁኔታም እየጠቃቀስን ለማሳያነት እናስታውስ።

**የሥነ ምግባርና ሥነ ዜጋ ውድቀታችን፤**

ቀዳሚዎቹ የሀገራችን ሁለት ሙት ሥርዓቶች (ደርግና ኢሕአዴግ) ዘርተውና ኮትኩተው የተንከባከቡት “እርግማን” እነሆ ዛሬ አዝመራው ነጥቶ ፍሬው በየቤታችን ለመዘመር በቅቷል። ግራ ገቡና ኮሚኒስት ነኝ ባዩ የደርግ ሥርዓት የሃይማኖትንና የነባር ሥነ ምግባር ፋይዳን በማጥላላት “ትውልድ የሚያደነዝዙ ኮኬይን ናቸው” በማለት በመርህ ደረጃ ያራመደው ፍልስፍና ብዙው ዜጋ “ለሃይማኖት ጥዩፍ፣ ለፈጣሪ ደንታ ቢስ” እንዲሆን ምክንያት ሆኖ ነበር። አልፎም ተርፎ በመንግሥት ሚዲያም ሳይቀር ይሄው ጥላቻ በግልጽ ይንጸባረቅ እንደነበር የወቅቱ የኢትዮጵያ ፕሬስ መምሪያ ኃላፊ የነበሩት አቶ ሙሉጌታ ሉሌ(?) (ዮሐንስ ሙሉጌታ በሚል የብዕር ስም) “አጥፍቶ መጥፋት” በሚል ርዕስ ባስነበቡን መጽሐፍ ውስጥ እማኝነታቸውን የሰጡት እንዲህ በማለት ነበር።

“ማስታወቂያ ሚኒስቴርን ሕዝቡ በመንግሥት ዐይን በማየት ‹ማስታወኪያ ሚኒስቴር› ሲለው ኖሯል። … ፓርቲው (አሠፓ) እና መንግሥቱ በሚከተሉት ርዕዮተ-ዓለም የተነሣ ሚዲያዎቹ በሚያስተላልፏቸው ፕሮግራሞች፣ ዜናና ሀተታ አማካይነት ሃይማኖቶቹን ጎነጥ ሳያደርጉ አያልፉም። ሌላው ቀርቶ በበዓላት ቀናት፤ “እንኳን ደረሳችሁ” ማለት ተለምዶ ነበር። “አደረሳችሁ” ከተባለ በውስጡ አምላክን የሚጠራና የሚያመሰግን መልዕክት ስላለው “ደረሳችሁ” መደበኛ ቋንቋ ወደ መሆን ደርሶ ነበር። አክራሪ ካድሬዎቹም “እንኳን ደረስህ” ሲባባሉም መልሱ “በትግሌ” ሆኖ ነበር” (ገጽ 112-113)።

የደርግ መንግሥት በዋና ዋና የሃይማኖት መሪዎችና በአማንያኑ ላይ ይፈጽም የነበረውን እስከ ግድያ የሚደርስ እጅግ ዘግናኝ ግፍ፣ የአምልኮ ሥፍራዎቻቸውንና የማሕበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማቱን በመውረስ ጭምር የወሰዳቸውን እኩይ እርምጃዎች በተመለከተ ይህ አምደኛ “ኤሎሄ እና ሃሌ ሉያ” በሚል ርዕስ በ1992 ዓ.ም በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ዝርዝሩን በሚገባ ለማሳየት ሞክሯል።

ፀረ አምላክና ፀረ እምነት የሆነው የደርግ መንግሥት መናድ የጀመረውን የሃይማኖትና የሥነ ምግባር እሴቶች እጅግ በረቀቀ ስልት እንዳያንሰራራ በማድረግ ያጠናከረው በርዕዮተ ዓለም ፍልስፍናው ከደርግ ያልተሻለው “ኮሚኒስት ነኝ” ባዩ የኢህአዴግ ሥርዓት ነበር። የኢህአዴግ ሃይማኖት ጠልነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ሥርዓተ ትምህርቱን ቀርጾ የተገበረው ፈሪሃ አምላክ እምነት እንዳይኖርና በጠንካራነት የሚገለጹት ነባር የማሕበራዊ እሴቶች አብረው እንዲከስሙ በማድረግ ጭምር እንደሆነ የግል እማኝነትን ዋቢ በማድረግ አስረግጦ መናገር ይቻላል። የአደባባይ ግልጽ ሌብነት፣ ዘረፋ፣ ሙስና፣ ለመደበኛ ሥራ የሚሰጥ ደካማ ግምት፣ በአቋራጭ ለመክበር የሚደረግ ሩጫ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ የሚታየው ግዴለሽነት ወዘተ. ለሥነ ምግባር መራቆት ግርድፍ ማሳያዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ስለዚህ የዛሬዎቹ አብዛኞቹ ወላጆችም ሆኑ ልጆች በእነዚህ ሁለት ሥርዓቶች ውስጥ ተወልደው ያደጉ ስለሆነ “ሃይማኖታዊ እምነት” የፌዝ ያህል እንዲቀልና ግብረገብ ይሉት እሴት ደብዛው እስኪጠፋ ድረስ የልጆች አስተዳደግና አመራር ዘይቤያችንና የአኗኗራችን መርህ ግለኝነት የተማከለበት “ኬሬዳሽ እና ‹ምንተዳዬ›” ይሉት ዓይነት ሊሆን ግድ ሆኗል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ (ዶ/ር) ከጥቂት ቀናት በፊት ከመላው ሀገሪቱ ከተውጣጡ ወጣቶች ጋር ባደረጉት ውይይት ላይ ወጣቱ “ፈሪሃ ፈጣሪ” እንዲያድርበት አጥብቀው የመከሩት ይሄው ሀገራዊ ድቀታችን በእጅጉ ስላሳሰባቸው ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል።

**ልጆቻችንን ምርኮኛ ያደረገው ቴክኖሎጂ፤**

ዓለማችን እንቅልፍ አጥታ በየእለቱ እያበረከተችልን ያለው የቴክኖሎጂ ውጤቶችና የማሕበራዊ ሚዲያው ጉዳይ ለራሷ ለሰጭዋ ዓለማችን ሳይቀር “ላም እሳት ወለደች፤ እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ልጅ ሆነባት” እንዲሉ የበረከተ መርገምትነታቸው ውጤት በይፋ መገለጥ ከጀመረ ዓመታት ነጉደዋል። የዘመኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለምድራችን አዳሜና ሔዋኔ የሰው ዘሮች ሕይወትን በማቅለሉ ረገድ ያበረከታቸው አስተዋጽኦዎች በእጅጉ የሚመሰገኑ መሆናቸው በፍጹም የሚካድ አይደለም። የቴክኖሎጂው ትሩፋት ዓለም በጣታችን ውስጥ እንድትገባና አኗኗራችን በብዙ ዘርፍ “የገለባ ያህል እንዲቀል” ማድረጉን ለመካድም ሆነ ለመጠራጠር በፍጹም አይቻልም።

ችግሩ ከበረከቱ እኩል የመርገምትነቱ ጉዳይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶ እየገዘፈ መሄዱ ላይ ነው። በከተማም ይሁን በገጠር በሚገኙት ልጆቻችን ዘንድ ያለ ማሕበራዊ ሚዲያ ተግባቦት ለመኖር እየተቸገሩ ብቻም ሳይሆን ለመኖር ከሚያስፈልጉ መሠረታዊ ጉዳዮቻችን (መብላት፣ መልበስ፣ መጠለል ወዘተ.) እኩል ዋጋው ከፍ ያለ ወደ መሆን ደረጃ ተሸጋግሯል። ግንኙነቱ ለመልካምነት፣ ለበጎነትና ለትምህርት ቢውል ኖሮ ባልከፋ፤ ችግሩ ከዚያም ገዝፎ በሕይወታቸው ላይ የሚፈጽመው ጫናና አሉታዊ ባህርያት መበራከቱ ላይ ነው።

በፌስ ቡክ፣ በዩ ቲዩብ፣ በቲክ ቶክ እና በበርካታ “እድፋም ማሕበራዊ ድረ ገጾች” አማካይነት ሥነ ምግባርንና ማሕበራዊ መስተጋብርን በማንኳሰስና በመዳፈር ለልጆቻችን እየጎረፉ ያሉት በጎ ያልሆኑ መልእክቶችና “አድርጉና ሞክሩት” እየተባሉ ለግብዣ የሚቀርቡላቸው “መርዞች” የስንቶቹን ልጆቻችንን ሕይወት እንዳበላሹና ለአደጋ እንደጋረጡ ለወላጆች ይጠፋል ማለት አይቻልም። ከተፈጥሯዊ ማሕበራዊ ግንኙነት እያራቋቸው፣ ለብቸኝነትና ለድብርት እየዳረጓቸው፣ በአልተፈለጉ “እርኩሰታዊ” ልምምዶች እየዘፈቋቸው እንዳሉ ፍሬያቸው በግልጽ እየተገለጠ ነው።

እርግጥ ነው አብዛኛው የመደበኛ ትምህርቶች አሰጣጥ “ቨርቹዋል” ወደሚሰኘው አተገባበር እየተሸጋገረ እንዳለ የሚካድ አይደለም። የመማሪያና የመርጃ መጻሕፍት፣ የቤት ሥራዎች፣ ለተጨማሪ የዕውቀት ግብዓቶች የሚያግዙ መረጃዎች፣ የምርምር ሥራዎችና ፈተናዎች ወዘተ. ሳይቀሩ በሙሉ የመገኛ ምንጫቸው ቴክኖሎጂው ጎራ ተጠቅልሎ እየገባ መሆኑ አይካድም። ደግመን እንላለን እነዚህ ሁሉ መልካም እድሎች የትምህርቱንና የምርምር ድካምን ስለመቀነሳቸው መካድም ሆነ ለክርክር ማቅረብ በፍጹም የሚቻል አይደለም።

ችግሩ ከእነዚህ መልካም ተግባራቱ ጎን ለጎን የሚጎርፉት ሥነ ምግባር የጎደላቸው መልእክቶችና ተግባራት በልጆቻችን ላይ የሚፈጥሩት ጫና፣ ሥነ ልቦናዊ ቀውስና መጥፎ ልምምዶች እንዴት ሊታረሙ ይችላሉ የሚል ነው። በእጅ ስልካቸው ላይ ተጥደው የሚውሉት ልጆቻችን ብቻም ሳይሆኑ መምህራንና ወላጅ ተብዬዎችም የዚሁ “ዘመን ወለድ” ችግሮች ተጠቂዎች መሆናችን የሚካድ አይደለም። ርእሰ ጉዳዩ በልጆቻችን ላይ ብቻ ስላተኮረ እንጂ ወላጆችንና መምህራንን በሚመለከቱ መሰል ጉዳዮች ላይ ወደፊት በስፋት መመለሳችን አይቀርም።

የሶሻል ሚዲያው በጎ ያልሆነ ተጽእኖ በዛሬዋ ዓለም በወጣቶች ላይ እያሳደረ ያለው ጉዳት እየተነጻጸረ የሚገለጸው “ድምጹን በማጥፋት የማሕበረሰብን በጎ እሴቶች እንደሚያወድም አጥፊ የኒኩሌየር አረር” ነው። በማሕበራዊ መረብ ግንኙነት (chat) ሱስ የተጠመዱ ታዳጊዎችና ወጣቶች ብዙውን ጊዜ ከቤተሰባዊ ተሳትፎ ርቀው ብቸኝነትንና መገለልን መምረጣቸው የቤታችን ገመና የሸሸገው እውነታ ነው። አላግባብ የሚገድሉትን ጊዜያቸውን እያሰቡና “የሚዘፈቁባቸውን አይረቤ የስሜትና የሥነ ልቦና ማጦች” መለስ ብለው ሲመረምሩም በጸጸት ስለሚቀጡ ለበርካታ የፋይናንስ ቀውስና የጤና ችግሮች እንደሚዳረጉ ጥናቶች በስፋት እያረጋገጡ ነው።

እንቅልፍ ማጣት፣ ድብርት፣ በትምህርት አቀባበል ደካማ መሆን፣ ለሀሰተኛ ዜናዎችና መረጃዎች መጋለጥ፣ የበታችነት ስሜት፣ ለፍቅር ግንኙነት የተሳሳተ ግምትና እምነት ማሳደር፣ በመንፈሳዊ አምልኮ ስም ወደ ተሳሳቱ ልምምዶች መግባት ወዘተ. በመጨረሻም “ራስን በአይረቤነት ፈርጆ” ያልተገቡ እርምጃዎችን እስከ መውሰድ መድረስ በአጥኚዎቹ ውጤት የተረጋገጡ ዋና ዋና ማሳያዎች ናቸው።

ሚዛናዊነት የጎደለው የልጆቻችን የሶሻል ሚዲያ አጠቃቀም አሉታዊ ተጽእኖ ሙሉ ለሙሉ ተጠንቶ ተጠናቋል ለማለት ስለማያስደፍር ገና ብዙ ሊተኮርበትና ሊሰራበት እንደሚገባ ይታመናል። “ቴክኖሎጂው የዘመኑ ትሩፋት ስለሆነ ምን ማድረግ ይቻላል?” ከሚለው ከዳተኛነት አስተሳሰብ በመላቀቅ በልጆቻችን የማሕበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ላይ በጊዜ የተወሰነ ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ከወላጆች እንደሚጠበቅ የዘርፉ ተመራማሪዎች አጽንኦት ሰጥተው መምከራቸው አልቀረም።

ልጆቻችን “ስማርት ስልክ ግዙልኝ!?” ብለው ሲጠይቁን “ምንገዶኝ! እኔ እንዳደኩት ልጄ ማድግ የለበትም” በሚል የቁጭት ውሳኔ ወላጆች ተገፋፍተው ለችግሩ ምክንያትና ሰበብ እንዳይሆኑ አጥብቀው ቢያስቡበት እንደሚበጅም ተደጋግሞ ይገለጻል። በሀገራችን ዐውድ እንደሚታየው ጡት የሚጠቡ ሕጻናት ሳይቀሩ ሲያለቅሱ ዝም ለማሰኘትና ለማባበል የሚሞከረው የእጅ ስልክን በመስጠት እስከ መሆን ተደርሷል። “በዕንቁላሉ ጊዜ” ያላረምናቸው ልጆቻችን “በበሬ ልክ የሚገመት ጥፋት” ሰርተው ሲጎዱና ማሕበረሰቡን እስከ መጉዳት ሲደርሱ ከመፀፀት ይልቅ ገና ከማለዳው ከጎናቸው ቆመንና እኛም አርአያ ሆነናቸው ወደ “ቀናው መንገድ” ብንመራቸው የተሻለ ይሆናል።

ይህ ዘመን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዘመኑን የሚዋጅ የሥነ ምግባር መገንቢያ የግብረገብ ትምህርት ለልጆቻችን የሚያስፈልግበት ወቅት ነው። የሃይማኖት ተቋማትና “ለሰብዓዊነትና ለበጎነት” ቆመናል የሚሉ ድርጅቶች ይህንን ችግር ልብ ተቀልብ ሆነው ቢያስቡበት ይበጀናል። አየሩ ላይ የናኙት የሀገራችን የሚዲያ ተቋማትም በርብርብ ከወላጆች ባልተናነሰ ድርሻ ችግሩ ላይ ለመዝመት የገዘፈ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሊረዱት ይገባል። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን “ፈጣሪን ፍሩና ታዘዙ” በማለት ለወጣቶች እንዳስተላለፉት ዓይነት መልእክት ደግሞ ደጋግሞ ከሃይማኖት መሪዎችና ከታላላቆች መስተጋባቱ እጅግ አስፈላጊና ተገቢም ነው።

የኪነ ጥበቡ ሰፈር፣ የትምህርት ሥርዓቱና የተለያዩ ማሕበራዊ መድረኮች (ስፖርት፣ ስካውት፣ ልዩ ልዩ የወጣቶች ተሳትፎ ወዘተ.) ርብርብ በማድረግ ለልጆቻችን ስኬት እንድንዘምር እንጂ ጉዳታቸውን እያየን እንዳናለቅስና እንዳንቆዝም ሊያግዙን ይገባል። ፍሬያማ ድርሻቸውን በመወጣትም የወላጆችን ጭንቀት እንዲጋሩ የትውልዱን አደራ በትከሻቸው ላይ ማስቀመጡ ተገቢና አስፈላጊ መስሎ ታይቶናልና መልእክታችን ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ይድረስልን እንላለን። ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## የቁም እንስሳት ግብይትን የማዘመን ፋይዳ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ታድላለች። አገሪቱ በአፍሪካ ግንባር ቀደሚ፣ በዓለምም ተጠቃሽ ከሚባሉት አገሮች ተርታ እንደምትመደብ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ሀብቷን መጠቀም እንዳልቻለችና በተለይም ከምርትና ምርታማነት፣ ከግብይት፣ ከጥራት አንጻር የእንስሳት ዘርፉ ችግር እንዳለበት መረጃዎች ያመለክታሉ። አገሪቷ በተፈጥሮ ከታደለችው የእንስሳት ሀብቷ ተጠቃሚ መሆን ካልቻለችባቸው በርካታ ምክንያቶች መካከልም ሕገ ወጥ ንግድ፣ የጥራት ጉድለት፣ የእርድና የትራንስፖርት አገልግሎት ችግር፣ የፋይናንስ አቅርቦት እና የእንስሳት ማቆያ ማዕከላት አለመኖር ይጠቀሳሉ።

ከግብይት ጋር ተያይዞ ከሚነሱ ችግሮች መካከል ሕገ ወጥ ንግድ በዋነኝነት ይጠቀሳሉ። በተለይ በግብይት ሥርዓት ወደ ኋላ የቀረች በመሆኗ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሬ እያገኘች አለመሆኗ ሁሌም ይገለጻል።

በኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን የአርብቶ አደር አካባቢ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንቅስቃሴና ተግዳሮቶች ላይ የተዘጋጀ መድረክ ሰሞኑን በተካሄደበት ወቅት በእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት የእንስሳት ምርቶችና መኖ ማቀነባበር ጥራት ዘርፍ አስተባባሪ አቶ ታሪኩ ተካ እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል።

እንስሳት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የማይሆኑት የለም የሚሉት አስተባባሪው፣ እንስሳት ምግብ፣ ገንዘብ፣ ጉልበት መሆናቸውን ያብራራሉ። ባህላዊ ምግቦች ጭምር የሚደምቁት ከእንስሳት በሚገኙ የተለያዩ ተዋጽኦዎች መሆኑን ያመለክታሉ። እንስሳት ለተለያዩ የገንዘብ ምንጮች ዋስትና በመሆን ለአርሶ አደሩ ባንክ ሆነው እያገለገሉ መሆናቸውን ነው የሚናገሩት።

እሳቸው እንዳሉት፤ የእንስሳት ሀብት በኢትዮጵያ በሚገባው ልክ መልማት ባለመቻሉ አገሪቷ ከዘርፉ መጠቀም የሚገባትን ያህል መጠቀም ባትችልም ዘርፉ ትልቅ አበርክቶ ያለው ስለመሆኑ ግን የማይካድ ሃቅ ነው፤ በኢኮኖሚ ተደራሽነቱም ቢሆን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ሲነጻጸር የእንስሳት ሀብት ከፍተኛ ድርሻ አለው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከ18 ሚሊዮን በላይ መሬት ያላቸው አርሶና አርብቶ አደር የሆኑ አባወራዎች ስለመኖራቸው ጠቅሰው፣ ከእነዚህም መካከል 14 ሚሊዮን የሚደርሱት አባወራዎች በየቤታቸው ቢያንስ አንድና ከአንድ በላይ የዳልጋ ከብቶች እንዳሏቸው አቶ ታሪኩ አስረድተዋል። ኢትዮጵያ ከምሥራቅ አፍሪካ በግመል ቁጥር ቀዳሚ ስለመሆኗ ያነሱት አቶ ታሪኩ፤ ስምንት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የሚደርሱ ግመሎች በኢትዮጵያ ውስጥ ስለመኖራቸው ነው የጠቀሱት።

በቆላ አካባቢ የሚኖረው የማኅበረሰብ ክፍል በእርሻ ብዙ የሚጠቀም እንዳልሆነም ተናግረው፣ በእንስሳት ሀብት ተጠቃሚ መሆኑን ይገልጻሉ። በአካባቢው የሚገኘው የእንስሳት ሀብትም በተፈጥሮ የታደለው እንጂ ለእንስሳት ሀብቱ ትኩረት በመስጠት በእንክብካቤና በክትትል እንዲሁም እንስሳቱን በማልማት የተገኘ ውጤት እንዳልሆነም ይናገራሉ።

ተገቢውን ትኩረት በመስጠትና በእንክብካቤ እንስሳቱን ማልማት ቢቻል ዘርፉ የአገሪቱ በርካታ ችግሮች መፍቻ ቁልፍ መሣሪያ ሊሆን የሚችል አቅም እንዳለው ተናግረው፣ የእንስሳት ሀብቱ ቢለማ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ትርጉም ያለው ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችል ነው ያስረዱት።

እንደ አስተባባሪው ገለጻ፤ በተለያየ ጊዜ በሚወጣው መረጃ መሠረት ከእንስሳት ሀብት ከፍተኛ ገቢ ማግኘት ይቻላል፤ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው የጎላ ነው። ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከ12 እስከ 19 በመቶ ድርሻ ይኖረዋል።

የግብርናው ብቻ ተነጥሎ ሲታይ ደግሞ የእንስሳት ሀብት 47 ከመቶ የሚሆን ድርሻ አለው። በአንሳት ሀብት ከሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በላይ በአገሪቱ ውስጥ የተመጣጠነ ምግብ ሲታሰብ እንስሳት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ። ከመቀንጨር ነፃ የሚያደርጉ የምግብ ዓይነቶች እንደ ወተት፣ እንቁላል፣ ስጋና ሌሎችም ሲታሰቡ የእንስሳት ጥቅም እጅግ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና ከቤተሰብ ሕይወት ጋር ያለው ጥብቅ ቁርኝት ከፍተኛ ነው።



**ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ከአፍሪካ አንደኛ፣ ከዓለም ደግሞ ተጠቃሽ ከሆኑ ጥቂት አገሮች መካከል አንዷ ብትሆንም፣ ከሀብቱ የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ ልትሆን አልቻለችም**

> **ይህን ችግር ለመቅረፍም አርብቶ አደሩ በኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅቶ ተጠቃሚ የሚሆንበት እና አገሪቷም ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ኮሚሽኑ በዋናነት እየሠራ ይገኛል፡፡ ለዚህም አምራችና ሸማቹን የሚያገናኝ ምቹ የገበያ መድረክ ለመፈጠር የታሰበ ሲሆን፣ በዚህ ላይም የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል**

እንስሳት ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው በበለጠ ከሰው ልጆች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው በመሆኑ በተለይም ሜካናይዜሽን ባልተስፋፋበት አገር ለግብርናው ዘርፍ ጉልህ ድርሻ አላቸው። አብዛኛው እርሻ፣ ውቂያና መንገድ ባልተስፋፋበት አካባቢ ደግሞ ትራንስፖርትና ሌሎች ሥራዎችም በዚሁ የእንስሳት ዘርፍ የሚሸፈን ነው። በእነዚህና መሰል ምክንያቶች የተነሳ እንስሳት ለሰው ልጆች የሚሰጡት አገልግሎት በገንዘብ ከሚተመነው ዋጋ በላይ ይሆናል።

በአርብቶ አደር አካባቢዎች እንስሳት ማለት የኩራትም የክብርም ምንጮች ስለመሆናቸው የሚናገሩት አቶ ታሪኩ፣ ኤክስፖርቱን የሚደግፍ በኢንዱስትሪዎችም በርካታ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል ሰፊ ዘርፍ ነው ሲሉ ያብራራሉ።

በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት ተጠቃሚ ለመሆን ችግሮቹን የመለየት ሥራ በሚመለከታቸው አካላት እየተሠራ መሆኑንም አስተባባሪው ይጠቅሳሉ። ዘርፉን እጅግ ከሚፈታተነው ሕገ ወጥ ንግድና ኋላ ቀር የግብይት ሥርዓት በተጨማሪ የእንስሳት ዝርያዎች አለመሻሻል፣ የመኖ እጥረት እና በእንስሳት ጤና አጠባበቅ ላይ ብዙም አለመሠራቱ የዘርፉ ቁልፍ ችግሮች መሆናቸውን ያብራራሉ።

ዘርፉ ዘመኑ የሚፈልገውን አገልግሎት መስጠት እንዲችል በዘመናዊ መንገድ መመራት እንዳለበት ያስገነዘቡት አቶ ታሪኩ፤ መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ከእንስሳት ሀብቱ የሰው ልጆች ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ ለማድረግ ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል። በተለይም በዘርፉ ሰፊ ዕውቀት ያላቸው ባለድርሻ አካላት ያላቸውን ሰፊ ዕውቀት መሬት በማውረድ አገሪቷ ከተትረፈረፈው የእንስሳት ሀብቷ ይበልጥ ተጠቃሚ እንድትሆን ይሠራል ሲሉም አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ አብዲ ሙመድ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ በቁም እንስሳት ምርት ከአፍሪካ አንደኛ ናት፤ ከዓለም ደግሞ ተጠቃሽ ከሚባሉት አገሮች መካከል ትገኛለች።

አቶ አብዲ አገሪቱ ከዚህ ሀብት ተጠቃሚ አለመሆኗን ጠቅሰው፣ ሀብቱን ከማልማትና ተጠቃሚ ከመሆን አንፃር አርብቶ አደሩ ከፍተኛ ውስንነት እንዳለበት ገልጸዋል። ለዚህም የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን በአርብቶ አደር አካባቢ የህብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀትና የተለያዩ ጥናቶችን በማድረግ ከክልሎች ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጉን አንስተዋል።

እንደ ምክትል ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ከእንስሳት ሀብቷ ተጠቃሚ መሆን ካልቻለችባቸው ምክንያቶች መካከል በግብይት ሰንሰለቱ የሚስተዋለው ችግር በዋናነት የሚጠቀስ መሆኑን እሳቸው መረዳት ችለዋል። አብዛኛው የቁም እንስሳት ሕዝቡም ሆነ አገሪቷ ሳትጠቀምበት ወደ ውጭ እንዲወጣ እየተደረገ ሌሎች አገራት የውጭ ምንዛሬ እያገኙበት ናቸው።

ይህን ችግር ለመቅረፍም አርብቶ አደሩ በህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅቶ ተጠቃሚ የሚሆንበት እና አገሪቷም ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ኮሚሽኑ በዋናነት እየሠራ ይገኛል። ለዚህም አምራችና ሸማቹን የሚያገናኝ ምቹ የገበያ መድረክ ለመፈጠር የታሰበ ሲሆን፣ በዚህ ላይም የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል።

የኢትዮጵያ ህብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ወይዘሮ ፍሬያለም ሸባባው በበኩላቸው፤ መንግሥት በአሁኑ ወቅት አርብቶ አደርና ቆላማ ተብለው የሚጠሩትን ክልሎች ትልቅ የኢኮኖሚ መሠረት ናቸው ብሎ የሚጠራቸው ክልሎች እንደሆኑ ገልጸዋል። እነዚህ አካባቢዎች ቀደም ሲል ድጋፍ የሚያሻቸውና ወደ ኋላ የቀሩ ተብለው ይታወቁ እንደነበር አስታውሰው፣ በአሁኑ ወቅት ግን ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ትልቅ መሠረት ከሆኑት አካባቢዎች መካከል ተጠቃሽ እንደሆኑ አስታውቀዋል።

እንደ ኮሚሽነሯ ገለጻ፤ በእነዚህ አካባቢዎች በዋናነት ምን ይመረታል? በማምረቱ ሂደት ምን ዓይነት ችግሮች ይገጥማቸዋል? ተደራጅተዋል ወይ? በአካባቢያቸው የሚፈጥርባቸው ተጽዕኖዎች እንደምን ያሉ ናቸው? ለምሳሌ ድርቅ በየጊዜው በሚያጠቃቸው አካባቢዎች ምን ዓይነት ዝግጅት መደረግ አለበት? ከአርሶና አርብቶ አደሩ ምን ይጠበቃል? ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ ምን መደረግ አለበት? የሚሉ በርካታ ሥራዎች በኮሚሽኑ በኩል እየተሠሩ ናቸው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በሕገ ወጥ ንግድ በከፍተኛ ደረጃ ሰለባ የሚሆኑት በእንስሳት እርባታ የተሰማሩ አርብቶ አደሮች ስለመሆናቸው ወይዘሮ ፍሬያለም ጠቅሰው፤ እነዚህ አርብቶ አደሮችም ለሕገወጥ ንግድ፣ አስፈላጊ ላልሆነ የድንበር ላይ ንግድ ይጋለጣሉ ብለዋል።

በአገሪቱ በሚስተዋለው ኋላ ቀር የግብይት ሥርዓት በተለይም አርብቶ አደሩ ተጎጂ ነው ያሉት ኮሚሽነሯ፤ አርብቶ አደሩ በለፋበት ሌላው ምንም ዓይነት እሴት ያልጨመረው ሕገ ወጥ ነጋዴ ተጠቃሚ ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል። አብዛኞቹ አርብቶ አደሮችም ለሕገወጥ ንግድ በመጋለጥ ለከፍተኛ ምዝበራ መደረጋቸውን ይጠቅሳሉ።

ኮሚሽነሯ እንደሚሉት፤ አካባቢዎቹም ጠረፍ አካባቢ መገኘታቸውም ለዚሁ ሕገ ወጥ ንግድ ተጋላጭ ሆነው ይገኛሉ። ሌሎችም እንዲሁ በእንስሳትና በማዕድን ንግድ ላይ የተሰማሩ ማህበራት ዘመናዊ የንግድ አሠራር ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ለችግሮች ተጋፍጠዋል።

አርብቶ አደሮች አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ባለመቻላቸው፣ የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አቅርቦት ባለመኖሩ፣ የማስቀመጫ እና ሌሎችም ችግሮች ያሉባቸው መሆኑን ኮሚሽኑ መረዳቱን ጠቅሰው፣ ችግሮቹን ለመፍታት የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ እንደሆነም ተናግረዋል።

«ኮሚሽኑ ከክልሎች ጋር በተናጠል ባደረገው ውይይት በርካታ መረጃዎችን አግኝቷል» ያሉት ኮሚሽነሯ፤ ምርቶችን እንደገና በአዲስ አይታ ለማየት ሰፋ ያለ ውይይት መደረጉንም አስታውቀዋል። በተገኘው መረጃ መሠረትም የአርብቶ አደር አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ ምርት የሚገኝባቸው ክልሎች ስለመሆናቸው መለየቱን ጠቅሰዋል። የአርብቶ አደሮቹ የማምረት አቅም ከአገር ውስጥ አልፎ በውጭ ገበያ ተደራሽ በመሆን ትልቅ ተጽእኖ መፍጠር የሚችሉ የምርት ባለቤቶች እንደሆኑም ተናግረዋል።

ነገር ግን የቁም እንስሳትን ጨምሮ የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ሂደት ያለው የግብይት ችግር ፈታኝ እንደሆነ በማንሳት አርብቶ አደሮቹ፤ ከማስቀመጫ ቦታዎች ጀምሮ የተለያዩ ችግሮችን እየተጋፈጡ እንደሆነ ኮሚሽኑ መረዳት እንደቻለ ጠቅሰው፣ እነዚህን የተለያዩ ችግሮች በዘላቂነት ለመፍታት የአርብቶ አደሩ ድርሻ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ መንግሥት አርብቶ አደርና ቆላማ ቦታዎችን በከፍተኛ ደረጃ ለማልማት እየሠራ ነው። ማልማት ሲባልም አንዱና ቀዳሚው መሠረተ ልማት ማሟላት ነው፤ ለአብነትም በሶማሌ ክልል በነበረ ውይይት የካርጎና የማቆያ ችግር መኖሩን መረዳት ተችሏል፤ እነዚህን ችግሮች በመቅረፍም ትላልቅ የትራንስፖርት ወጪዎችን መቀነስ ይቻላል።

ሌሎችም በማህበራት ተደራጅተው የአቅም ውስንነት ያጋጠማቸው እንዲሁም የአርብቶ አደር ፋይናንስ ያጋጠማቸው ለአብነትም የብድር አገልግሎት ያጡ ስለመኖራቸውም ጠቅሰው፣ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት እየተሠራ ነው ብለዋል።

የአርብቶ አደር ልማት ተብሎ ሲታሰብ ቀዳሚ የሚሆነው ሀብቱን እንዴት እናስተዳድር የሚለው ነው። ስለዚህ ያለንን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ለክልሎች አቅም በመጨመርና በማገዝ መሥራት ያስፈልጋል። ያሉት ኮሚሽነሯ፤ በተለይም የግብይት ሥርዓቱን ዘመናዊ በማድረግ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ገበያ አላስፈላጊ የሆኑ ሕገ ወጥ ንግዶችን ለመከላከል የሚሠራ መሆኑን ገልጸዋል። በቀጣይ ችግሮችን በመቅረፍ ምቾት ያለውና ጤናማ የሆነ የግብይት ሥርዓት ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ሀምሳ ሳንቲማችን ወደ ሶስት ብር አደገ

**ተገኝ ብሩ**

ከዓመት በፊት የሰማሁት ገጠመኝ ነው። አንዱ ታክሲ ተሳፍሮ ወደ ሚፈልግበት ይሄዳል። ረዳቱ ሂሳብ ሲጠይቀው አስር ብር አውጥቶ ይሰጠዋል። ነገር ግን ረዳቱ ወዲያው መልስ ከመስጠት ይልቅ ዝም ይለዋል። ልጁ በትዕግስት እጁን ዘርግቶ ጠበቀ። ረዳቱ ባላየ አለፈው።

ጎበዝ! የታክሲ ረዳቶች ይሄ ክፉ ልማድ የሚለቃቸው መቼ ይሆን? መልሱን በትዕግስት ይጠባበቅ የነበረው ተሳፋሪ ትንሽ ቆይቶ ‹‹እባክህን መልሴን ስጠኝና እሱን ማሰቡ ትቼ ሌላ ነገር ላስብበት›› ብሎ ተሳፋሪውን አስፈግጓል።

እነዚህ ታክሲዎች ዛሬም ታክሲ ውስጥ ሌላ ሀሳብ እንዳናስብ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል። ኑሮ ተወዶብን የለ! የቀኑን ግማሽ የምናሳልፈው ኑሮን በምን አይነት አስማት እንደምንመራ እያሰብን ነው። አንዳንዴማ ምን ይታሰበኛል መሰላችሁ፤ ይሄ ብዙ ሰዓት ቁጭ ብለን ኑሮን እንዴት እንምራ፣ ገቢያችንን እናሳድግ፣ አሁን ያለውስ በምን መልክ እንዲበቃን እናድርግ ብለን በትካዜና ሀሳብ የምናሳልፈው ረጅም ሰዓት ነው። ገቢና ወጪያችን አልመጣጠን ሲል በዚህ መልክ በግራ መጋባት ስሜት ለረጅም ሰዓት የምናስብበት ጊዜ ሀሳቡን ትተን በስራ ላይ ብናውለው ኑሮው አይቀልም ይሆን? እላለሁ።

በወርሀዊ ገቢ ወይም በደመወዝ የሚተዳደር ግለሰብ፤ ወጪው ለወር እንዲሆን አድርጎ መጠቀም ካልቻለ አኗኗሩ ላይ እክል ይፈጠርበታልና በየወሩ ወጪና ገቢውን ማስላቱ አይቀርም። በተለይ አብዛኛው ከተሜ ከወርሀዊ ወጪው ጋር አብሮ የሚያሰላው የትራንስፖርት ወጪ ለእኔም መሰረታዊ ጉዳይ ሆኗል።

በተለይ በመዲናችን በቋሚነት ለሚኖር እናም ትራንስፖርት ለሚጠቀም ሰው ለዚያ የሚሆን ወጪ መመደብ ግድ ይለዋል። ለዚያውም ከመጠባበቂያ

> **ታክሲዎች በመደበኛነት ያስመስመር መስራት፣ ተሳፋሪን መሳደብ፣ ሰዎችን መበደል ስራቸው፣ የሰዎች መብት ማጉደል ተግባራቸው፣ ህግ መጣስ መደበኛ ስራቸው ሆኗል**

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇

ጋር። መጠባበቂያ ያልኩት በምክንያት ነው። ታክሲዎች በታሪፍ ሳይሆን በፈለጉት ዋጋ ካልሆነ አንጭንም ስለሚሉ ነው። ዛሬ ላይ ታክሲዎች በተተመነላቸው ሳይሆን ደስ ባላቸው፤ በተፈቀደላቸው መስመር ሳይሆን ባመቻቸው መሄድ ተላምደዋል። ለእነሱ ደንበኛ የሚባል ንጉስ ተገልጋይ የሚባል ክብር ሊሰጠው የሚገባ ግለሰብ የለም።

ታክሲዎች በመደበኛነት ያለመስመር መስራት፣ ተሳፋሪን መሳደብ፣ ሰዎችን መበደል ስራቸው፣ የሰዎች መብት ማጉደል ተግባራቸው፣ ህግ መጣስ መደበኛ ስራቸው ሆኗል። እንደው ጎበዝ እዚህች ከተማ ላይ ከታክሲዎች በላይ ህግ የሚጥስ ከታክሲ ተጠቃሚ በላይ መብቱ የሚነጠቅ አለ ይሆን?

አሁን ላይ በተለይ የታሪፍ ጭማሪውን ሰበብ አድርገው የዘረፉ ያህል የፈለጉትን ተምነው ነው የሚጭኑት። አመሻሽ ላይ ‹‹ካዋጣህ ግባ ካልሆነ እንዳትገባ›› ይላሉ። የታክሲ ተራ አስከባሪዎች ስርዓትና ደንብ መጣሱ ግድ አይሰጣቸውም። ጠብቀው ሲሞላ ገንዘብ ከመቀበል ውጪ ሌላ ተግባር የላቸውም።

አሁን አሁን ታክሲ ውስጥ መልስ ስጠኝ ብሎ ረዳቱን መጠየቅ ከብዷል። ጎበዝ የታክሲ ረዳቶች ግን ስለሚያከብሩን ይሆን እንዴ መልስ የማይሰጡን። አንዳንድ የተላመዱን አራዶች ወይም መልዕክት የላከናቸው ህፃናት አንድ ነገር ተገልግለን ለዚያ የሰጠነው ክፍያ መልስ ካለውና መልሱን ላለመመለስ ሲፈልጉ “ለትልቅ ሰው መልስ አይሰጥም” ብለው ይቀልዱና መልሱን ያስቀራሉ።

ታክሲዎች ልክ እንደዚያ ትልቅ ናችሁ አንመልስላችሁም እያሉን ከሆነ ክብር እየሰጡን ይሆን? አይ አይ ለእኛማ ክብር እንደሌላቸው በሚሰጡን ተገቢ ያልሆነ አገልግሎት በደንብ አሳይተውናል። ኧረ ተው ታክሲዎች ደንበኞችሁን አታማሩ፤ የእውነት አክብራችሁ አስተናግዱ። ተው የእናንተ መልስ ባለመስጠታችሁ ምክንያት ከሚደርስብን መበደል ክብሩ ቢቀርብን ይሻላል። አዎ ስለምናከብራችሁ ነው መልስ የማንመልስላችሁ ማለት አቁሙ።

አንድ ሰሞን ሁለት ብር ከሀምሳ ለነበረ ታሪፍ ሶስት ብር ሰጥተን መልስ አልመልስ ብለው ያስቸግሩን ነበር። እናም ዝም ሲሉን “ኧረ በህግ ሀምሳ ሳንቲማችን ስጡን” እያልን ታክሲ ላይ መልሳችንን ለመቀበል ስንሚገት የነበረውን አንረሳም። ዛሬ ይህ ጉዳይ በሌላ ክፍል ከፍ ብሎ ቀጥሏል። ሀምሳ ሳንቲሙ ሶስት ብር ሆኖ አድጎ። “አረ ሶስት ብራችንን ስጡን” በማለት ረዳቶቹ እንዲሰጡን መለማመጥ ከጀመርን ውለን አድረናል። የሰባት ብር መንገድ አስር ብር ሰጥተን ሦስት ብር መመለስ ትተዋል።

የተደረገው የታሪፍ ጭማሪ ታሪፍ ብቻ ሳይሆን የጨመረብን ሊመለስልን የሚገባው መልሳችንንም ነው። ረዳቶች ሞግተን በግድ ካልሆነ በቀር የሚወስዱብን ሆን ብለው ነው። ኧረ መልሴን ብለን የጠየቅን እደሆነ፤ የሚሰጠን ስለጠየቅነው አይኑን እያጉረጠረጠ ወይም በንዴት እያጉተመተመ ነው። ቅር እያለውና አምስት ብር በርቀት እንቁልልጭ እያለን ሁለት ብር አምጣና አምስት ብር ልስጥህ ካልሆነ ዝርዝር የለኝም ሊለንም ይችላል።

አስቡት ጎበዝ እኔ ዝርዝር ባለማዘጋጀቴ ምክንያት ሁለት ብር ከምሰጥህ ካንተ ከታሪፍ በላይ ሶስት ብር ተጨማሪ ልውሰድ እያለን ነው። በነገራችን ላይ በአጋጣሚ ረዳቱ “ጨዋ” ከሆነ ሳንቲም የለኝም ቆይ እሰጥሀለሁ ይልና በኑሮ የጦዘው ጭንቅላታችን ወደሌላ ሀሳብ ስንወስደው ዝም እንደምንለው ስለሚያውቅ ረስተን ስንወርድ ኪሱ ይከታል።

ወይ ጉድ ወገን አልበዛም ግን! እስኪ አስቡት እኛም 2 ብር ከሀምሳ ሳንቲም መንገድ መቶ ብር አውጥተን ዝርዝር የለኝም እንጂ እሰጥህ ነበር ብለን ትተን እንወርዳለን? እንዲህ ብናደርግ ረዳቱ ምን ሊለን እንደሚችል አስቡት። በፍፁም እነሱ ግን ሶስት ብራችን ዝም ካልን ዋጥ፤ እንካችሁ መልስ ስጡን ካልን ጭቅጭቅ ሆኗል ተግባራቸው።

እንደው ዘወትር የሚገጥመኝ የታክሲ ላይ ብልሹ ልማድ ጠቀስኩ እንጂ ልክ ያልሆነው ነገራችን በርክቷል። በእያዳንዱ ጉዳያችን ላይ የሚታየው ስርዓት አልበኝነት እንደ ማህበረሰብ ያለንበትን ቁመና በደንብ የሚመላከት ነው። ስርዓት አልበኝነት በየመስኩ እያፈጠጠ ሲሄድ ሰላም ይርቃል። ህገወጦች ተው ወደ ህጋዊነት ተመለሱ ባይ ሲጠፋ ህግ ደፍጥጠው በጉልበት የሚያድሩ ይበረክታሉ። ይህንን ለማረቅ ደግሞ እንደ ማህበረሰብ ተገቢ ያልሆነውን አይተን ከማለፍ ይልቅ የሚስተካከልበት መንገድ ጠቁመንና እንዲስተካከል የበኩላችንን ጥረት ብናደርግ መልካም ይሆናል።

ህግ ማክበር የስልጣኔ ምልክት የስርዓታዊ አኗኗር መሰረት ነውና እያንዳንዳችን በየተገኘንበት መስከ ህጋዊ ሰው ለመሆን እንጣር። ያኔ ነገሮች ሁሉ ይቀላሉ። ዛሬ አገራችን ላይ የሚታየው የቡድኖች ህግ መጣስ ምክንያት ከመነሻው ትንንሽ ህግ መጣሶች ሲፈፀሙ ዝም መባሉ ነውና መልካም ያልሆነውን ልማድ ከጅምሩ መግታት ይገባል። አበቃሁ ቸር ይግጠመን።

# ዓለም አቀፍ



## ዋሺንግተን ታይዋንን ማስታጠቅ እንድታቆም ቻይና ጠየቀች

ዋሺንግተን ታይዋንን ማስታስጠቋን የምትቀጥል ከሆነ እርምጃ እወስዳለሁ ስትል ቻይና አስጠነቀቀች።

የባይደንን አስተዳደር ዋሺንግተን 1 ነጥብ 1 ቢሊየን ዶላር የሚገመት የመሣሪያ ሽያጭ ለታይዋን ለማቅረብ የሀገሪቷን ሕግ አውጪ አካል ለመጠየቅ ማቀዱን ፖሊቲኮ አስነብቧል።

ይህን ተከትሎም በአሜሪካ የቻይና ኤምባሲ ቃል አቀባይ ሊዩ ፔንግዩ ዋሺንግተንን አስጠንቅቀዋል።

ቃል አቀባዩ የአሜሪካ ዕቅድ “የአንድ ቻይና”ን ፖሊሲ እንዲሁም በአሜሪካ እና በቻይና መካከል የተደረሱ ዲፕሎማሲያዊ ስምምነቶችን የሚጥስ ነው ብለዋል።

መሰል ስምምነቶች “ተገንጣዮችን ያበረታታሉ”፤ “በቀጣናው ያለውንም ውጥረት ያባብሳል”ም ነው ያሉት።

በመሆኑም አሜሪካ ከታይዋን ጋር ያላትን ወታደራዊ ግንኙነት እና የመሣሪያ ሽያጭ በአስቸኳይ ታቁም ሲሉ መጠየቃቸውን አር ቲ ዘግቧል።

ይህ ሳይሆን ቢቀር ግን ቻይና ሉዓላዊነቷን እና ደኅንነቷን ለመከላከል አስፈላጊ እና ጠንካራ እርምጃ እንደምትወስድ አስጠንቅቀዋል።

እንደ ፖሊቲኮ ዘገባ የባይደን አስተዳደር ለታይዋን የ355 ሚሊየን ዶላር ፀረ-መርከብ ሚሳኤሎች እንዲሁም የ85 ነጥብ 6 ሚሊየን ዶላር የዓየር መቃወሚያ ሚሳኤሎችን ለመሸጥ አስቧል ሲል ኤፍቢሲ ዘግቧል።

በተጨማሪም በ655 ነጥብ 4 ሚሊየን ዶላር የክትትል ራዳር ለማቅረብ ማቀዱም ነው የተሰማው።

## በኢራቅ የሺዓ መሪው ራሳቸውን ከፖለቲካ ማግለላቸውን ተከትሎ በተነሳ ብጥብጥ 15 ሰዎች ተገደሉ

በኢራቅ የሺዓ መሪው ሙክታዳ አል ሳድር ከፖለቲካ ራሳቸውን ማግለላቸውን ተከትሎ በተነሳ ግርግር አስራ አምስት ሰዎች ተገደሉ።በኢራቋ መዲና ባግዳድ የተነሳው ሁከት በጸጥታ ኃይሎችና በፖለቲከኛው ደጋፊዎች መካከል በተነሳው ግጭት ነው።

ኢራቅ ባለስልጣናት እንደሚሉት የሙክታዳ አል ሳድር ደጋፊዎች ተቃውሟቸውን ለማሰማት የፕሬዚዳንቱን ቤተ መንግሥት ጥሰው ከገቡ በኋላ በርካቶች መቁሰላቸውን ተናግረዋል።አለመረጋጋቱ የተቀሰቀው ሙክታዳ አል ሳድር ከፖለቲካው አለም ራሳቸውን ማግለላቸውን ማሳወቃቸውን ተከትሎ ነው።የኢራቅ ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚንስትር መረጋጋት እንዲሰፍን ጥሪ ያደረጉ ሲሆን በሌሎች ከተሞች በተፈጠረውም አለመረጋጋት ጦሩ ብሔራዊ የሰዓት እላፊ አውጇል።

የኢራቅ ጎዳናዎች በተዋጊዎች የተኩስ ልውውጥ የተሞሉ ሲሆን በቅርብ ዓመታት ውስጥ ከታየውም አስከፊው ነው ተብሏል።እነዚህ ውጊያዎች የተካሄዱት በከተማው አረንጓዴ ዞን ተብሎ በሚጠራውና የመንግሥት ህንፃዎች ና የውጭ ኤምባሲዎች በሚገኙበት አካባቢ ነው።

ግጭቱ የተፈጠረው ለሙክታዳ አል ሳድር ታማኝ በሆኑት ፒስ ብርጌድስ በተሰኘው ሚሊሻ እና በኢራቅ ጦር አባላት መካከል እንደሆነ የኢራቅ ደህንነት ባለስልጣናት አስታውቀዋል።በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተጋሩ ቪዲዮዎች አንዳንድ ተዋጊዎች በሮኬት የሚንቀሳቀሱ የእጅ ቦምቦችን ጨምሮ የከባድ መሳሪያ ልውውጥ እንደነበር ያሳያሉ።ይህንንም ተከትሎ ኢራን ከኢራቅ ጋር የሚያዋስናትን ድንበር የዘጋች ሲሆን ኩዌት ዜጎቿ አገሪቷን በአስቸኳይ ለቀው እንዲወጡ አሳስባለች።

የህክምና ባለሙያዎች እንደሚሉት 15 የሙክታዳ አል ሳድር ደጋፊዎች በጥይት ተመትተው ህይወታቸው ሲያልፍ ወደ 350 የሚጠጉት ተቃዋሚዎች ቆስለዋል ሲል ኤኤፍፒ ዘግቧል።የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ቃለ አቀባይ በኢራቅ የተከሰቱት ሁነቶች አስደንጋጭ መሆናቸውን ገልጻው “ሁከቱን ለማረጋጋት አፋጣኝ እርምጃዎች እንዲወሰዱ” ጥሪ አቅርበዋል ።

ጊዜያዊ ጠቅላይ ሚኒስትር እና የሙክታዳ አል ሳድር አጋር የሆኑት ሙስጠፋ አል ካዲሚ የካቢኔ ስብሰባዎች እንዲታገዱ ውሳኔ አሳልፈው ተጽዕኖ ፈጣሪ የሃይማኖት አባቶች ጣልቃ እንዲገቡ እና ብጥብጡን እንዲያቆሙ ተማጽነዋል። የሙክታዳ አል ሳድር ከፍተኛ ረዳት ለኢራቅ መንግስት የዜና ወኪል ኢ ኤን ኤ እንደተናገሩት ሁከቱ እና የጦር ውጊያው እስኪቆም ድረስ የረሃብ አድማ እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል።

ሙክታዳ አል ሳድር ራሳቸውን ከፖለቲካ ህይወት ለማግለል ውሳኔ ያስተላለፉትተቀናቃኝ የሺአ መሪዎች እና ፓርቲዎች የኢራቅን የፖለቲካ ስርዓት ለማሻሻል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ነው።

በጥቅምት ወር፣ ለሙክታዳ አል ሳድር ታማኝ የሆኑ እጩዎች በኢራቅ ፓርላማ ብዙ መቀመጫዎችን ቢያሸንፉም ነገር ግን መንግስት ለመመስረት በቂ መቀመጫዎችን ማግኘት አልቻሉም። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በኢራን ከሚደገፉ የሺዓ ቡድኖች ጋር ለመደራደር ፈቃደኛ ባለመሆናቸውም ለአንድ አመት ያህል የፖለቲካ አለመረጋጋት አስከትሏል።

ሙክታዳ አል ሳድር የኢራቅ ፖለቲከኛ እና የሚሊሺያ መሪ ሲሆኑ የሳድሪስት ንቅናቄ መሪ እንዲሁም ቀደም ሲል የአሜሪካ ጦር ኢራቅ ውስጥ በነበረበት ወቅት ይመሩት የነበረው ሚሊሻ ማህዲ ጦር ተተኪ የሆነው የሰላም ኩባንያዎች መሪ መሆናቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## መሪ ተዋናይ ፍቃዱ ተክለማሪያም (1948 – 2010 ዓ.ም)

ግርማ መንግሥቴ

መቸም "አንጋፋው የኪነጥበብ ባለሙያ፣ የመድረኩ ንጉስ ፍቃዱ ተክለማርያም ከዚህ አለም በሞት ተለየ"ን የሰማ ሁሉ፣ ወደደም ጠላም "ክው" ያላለ የለም፤ በተለያዩ መድረኮች የተመለከታቸው የፍቄ የተለያዩ ሰብእናዎች ሁሉ እየተግተለተሉ ወደ አእምሮው ጓዳ ያልመጡ፤ ወይንም የፍቄን ትወና በዐይነ ህሊናው ያላያቸው ... አለ ለማለት በእውነት ይቸግራል። ፍቄ አይደለም ላወቀውና ቀርቦ ላወራው ባጋጣሚ ላየው ሁሉ ትዝታው ከአይን የሚጠፋ አይደለም፡፡

የሰው ልጅ በምግብ እና ውሃ ነው የሚያድገው እንበል እንጂ የፍቄን ሁለገብ ትወናዊ ብቃት እየተመለከተ፤ በወከለው ገፀባህርይ(ያት) እየተመሰጠ የኖረን ትውልድ "በምን አደግህ?" ተብሎ ቢጠየቅ፤ ከእህል ውሃው ቀጥሎ ለመልካም እድገቴ የፍቃዱ ሙያዊ አለበት ቢል የማያስኬድበት ምክንያት የለም። አዎ፣ የፍቄን ስራዎች አይቶ መንፈሱን ያልመገበ አለ ለማለት ይከብዳል።

ቀጥለን ፍቃዱን ከራሱ ጋር፤ ፍቃዱን ከሙያው ጋር፤ ፍቃዱን ከሙያ ባልደረቦቹ ጋር፤ ፍቃዱን ከአጠቃላይ አድናቂዎቹ ጋር፤ ፍቃዱን ከህዝቡ ጋር እያዛነቅን እንመለከታለን።

በአገራችን የትያትር ፍቅር እየጎለበተ የመጣው በፍቃዱና እንዲሁም ከፍቃዱ ትንሽ ቀደም ብለው በነበሩት በእነ አርቲስት ደበበ እሸቱ ዘመን እንደሆነ ይነገራል። የተለያዩ ጥናቶችም ይህንኑ ነው የሚያረጋግጡት። በመሆኑም ፍቄ ለጥበቡ ተመልካቾች ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ኪነጥበብ በአጠቃላይ፤ በተለይ ደግሞ ለትያትር ጥበብ እዚህ መድረስ የራሱን አሻራ (ሌጋሲ) አሳርፏል ማለት ነውና ፍቄ ባለውለታ ነው።

ፍቃዱ ተክለ ማርያም ለመጀመሪያ ጊዜ የመሪ ተዋናይነት ሚና ያገኘው በአባተ መኩሪያው "እሳት ሲነድ" በሚለው ቲያትር ሲሆን "እጅህን ስጥ አለኝ ፈረንጅ ..." የሚለውን የአጼ ቴዎድሮስ ንግግር ሲጀምር ተመልካቾች በዘመን ወደ ኋላ ሄደው የቴዎድሮስን ጀግንነት በእውንም እየተመለከቱ እስኪመስላቸው ድረስ አስቆዝሟል።

ፍቃዱን በሚገባ ይገልፀዋል ብለን ያሰብነው የቅርብ ወዳጁ የሆነዉ የብሔራዊ ትያትሩ አርቲስት ቴዎድሮስ ተስፋዬ ስለ ፍቄ የተናገረው ሲሆን፤ እሱም፣ «ፍቄ በሱ ዘመን የነበሩ የትያትር ባለሞያዎች አንዳንዶች ከሃገር ወጥተዋል፤ አንዳንዶቹም ከጥበቡ ርቀዋል፤ እሱ ብቻ ነው በዘመኑ ካሉት በሙያው የቀጠለው። ጥበብን የሚያከብር፤ እስዋ ራስዋ ጥበብ የምታከብረው በሰራቸው ስራዎች ሁሉ የማይኩራራ፤ አክብሮቱን ከትንሽ እስከ ትልቅ የሚገልፅ፤ ደከመኝ ሰለቸኝ የማይል፤ ሕዝብ በጠራው ቦታ የሚገኝ ሙያውን የሚወድና ሰውን የሚያከብር፤ ቤተሰቡን የሚወድ ሰው ነው ፈቃዱ። ፍቃዱ የኪነ-ጥበቡ አርማ ነው።» የሚለውና በተለያዩ ፅሁፎች ለንባብ የቀረበው ነው።

ብዙውን ጊዜ በመድረክ ላይ በንግሥናው፤ አልያም ደግሞ አፄ ቴዎድሮስን ሆኖ በመጫወት የሚታወቀው ፍቃዱ እጅግ ገናና ከሆነበት የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን "ቴዎድሮስ" ቴአትር በተጨማሪ በ"ኤዲፐስ ንጉስ"፣ "ሐምሌት" እና "ንጉስ አርማህ" ተውኔቶችም ንጉስን ሆኖ ተጫውቷል። በዚህም ምክንያት "ከመድረክ ጀርባ፤ ንጉሱ" የሚል መጠርያ እንደለውም አርቲስት ቴዎድሮስ ተስፋዬ ገልፆአል።

ይህንኑ ሀሳብም፣ በአንድ ስለ ፍቃዱ ሲባል በተዘጋጀ መድረክ ላይ «የተደረገው መነሳሳት እኔን ብቻ ሳይሆን መላውን የጥበቡን ቤተሰቦች እና ኢትዮጵያዊያንን ሁሉ ያስደሰተ ነገር ነው። ምክንያቱም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝቡ ከፍተኛ ርብርብ አድርጓል። ፍቃዱ እስከዛሬ በመድረክ ሙያው ላይ ያደረገውን አስተዋፅኦ በተመለከተ ሕብረተሰቡ ምላሽ እየሰጠ ይመስለኛል። ፍቅሩን እየገለፀለት ነዉ። ይሄ ደግሞ ለፍቃዱ የተደረገ ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም እንደተደረገ አድርጌ ነው የማየው።» ያለው ሌላው የመድረክ ንጉስ ደበበ እሸቱም በዚሁ አስተያየት እንደሚስማማ አርቲስት ቴዎድሮስ ተናግሯል።

አዲስ አባባ አራት ኪሎ አካባቢ ተወልዶ ያደገው፤ በ62 አመቱ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው መሪ ተዋናይ ፍቃዱ ተክለማሪያም መነሻው ቴአትር ቢሆንም በተከታታይ የቴሌቭዥን ድራማዎች (ለምሳሌ "ባለጉዳይ"፣ "ያልተከፈለ እዳ"፣ "የአበቅየለሽ ኑዛዜ"፣ "ገመና" ...)፣ በፊልሞች እንዲሁም በማስታወቂያ ሥራዎቹ እና በሬድዮ ትረካዎችም ጭምር አገር ያውቀዋል።



**ግንቦት 4 ቀን 2011 ዓ.ም በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በሚገኘው መካነ መቃብሩ ላይ የቆመውና ከ'ፋይበር ግላስ' የተሰራው የፍቃዱ ተክለማሪያም ሐውልት**

በ"ፀፀት" ፊልም ላይ ዳኛ ሆኖ የሰራው ፍቃዱ ዳኝነቱን እንደ ንጉስነቱ ሁሉ አሳምሮ የተጫወተው መሆኑን በወቅቱ የፊልሙ ደራሲ አቶ አለባቸው ደሳለኝ መስክረውለታል።

ከተሳተፈባቸው ወጥና ትርጉም ተውኔቶች መካከል ኦቴሎ፣ ኤዲፐስ ንጉሥ፣ ሐምሌት፣ ቴዎድሮስ፣ ንጉሥ አርማህ፣ መቃብር ቆፋሪውና የሬሣ ሳጥን ሻጩ፣ የሰርጉ ዋዜማ፣ አቡጊዳ ቀይሶ፣ ባለካባ ባለዳባ፣ መልዕክተ ወዛደር እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ:: ያልተከፈለ እዳ፣ ያበቅየለሽ ኑዛዜ፣ ባለጉዳይ እና የመሳሰሉት በህዝብ ዘንድ የሰረፁና አድናቆትን ያተረፉለት ስራዎቹ ናቸው::

በኢትዮጵያ ራድዮ ይተላለፍ የነበረው "ከመጻሕፍት አለም" ላይ ያቀርባቸው በነበሩ ትረካዎች በርካታ መጻሕፍት ላይ ህይወት ዘርቷል። "ምገደኛው ነውጤ"፣ "ጥቁር ደም"፣ "ሳቤላ"፣ "ወንጀለኛው ዳኛ" እና "ግራጫ ቃጭሎች" ከተረካቸው መጻሕፍት መካከል ይጠቀሳሉ።

በ1967 ዓ.ም በአዲስ አበባ ቲያትርና ባህል አዳራሽ ቅርብ ጓደኛው በነበረው ከሱራፌል ጋሻው ጋር የመቀጠር እድልን በማግኘት ዘርፉን የተቀላቀለው ፍቃዱ ለ42 ዓመታት ያህል በመድረክ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፤ አሁን ደግሞ በፊልም (ለምሳሌ "ቀይ ስህተት" በተባለው ፊልም የተዋጣለት ስራ ለመሥራት በመብቃቱ "አቶዝ" አውቶሞቢል የቴዲ ስቱዲዮ ሽልሞታል።) በርካታ ፈታኝ ሚናዎችን እየወከለ ተጫውቷል፡ ፡

ለ42 ዓመታት በርካታ የመድረክ ጥበብን በሙሉ አቅሙ ሲጫወት የኖረው አርቲስት ፍቃዱ ተክለማሪያም ባደረበት የኩላሊት በሽታ ሳቢያ ውጪ አገር ሄዶ ለመታከም ገንዘብ ቢሰበሰብለትም ከተሰበሰበው ገንዘብ 200ሺህ ብር "ከእኔ እሷ ልጅ ነች። ብዙ መኖር ያለባት እሷ ነች። እኔ ብዙ አይቻለሁ።" በሚል እሳቤ ለአንዲት ኩላሊት ታማሚ፤ በዚሁ ምክንያትም ትምህርቷን ከ10ኛ ክፍል ያቋረጠች ልጅ አበርክቷል። ሌላውና ፍቄን ለየት የሚያደርገው አንዱ ይህ በጎ ተግባሩ ነው።

### ሜላት አሰፋ ምን ትላለች?

ያኔ የፍቃዱ ጥሪ የመጣልኝ በጌታነህ ጸሀዬ በኩል ነበር። ገንዘቡን የሰጠኝ ምንም ባልጠበቅኩበት ወቅት ነበር። በሰዓቱ እጄ ላይ ብር አልነበረኝም። ሲጠራኝ እንዲሁ ሊያናግረኝ የፈለገኝ ነበር የመሰለኝ። መልካም ነገር ነው ያደረገልኝ፤ አመሰግነዋለሁ። በኛ ሀገር የኩላሊት እጥበት ወጪ ከባድ ነው። እሱ ግን ረዳኝ። ከሀገር ውስጥም ከውጪም ሰዎች ባሰባሰቡልኝ ገንዘብ እየታከምኩ ነው። አሁን በኮርያ ሆስፒታል የኩላሊት እጥበት እየተከታተልኩ ነው። ከረዳኝ በኋላ በስልክ እንገናኝ ነበር። ለመጨረሻ ጊዜ የተነጋገርነውን አስታውሳለሁ። 'በርቺ' የሚል ቃል ነበር የተናገረው። 'እንድናለን' ይለኝ ነበር። ድኖ እንገናኛለን ብዬ ነበር። ነገር ግን አልሆነም። (እዚህ ጋ ዮርዳኖስ "ፍቄ ከምንም በላይ አባት ነው። የሁሉም ሰው አባት ነው።" ያለውን ስክት ሲል እናገኘዋለን።)

### የፍቃዱ መታመምና የሕዝቡ ምላሽ

ሀይማኖቱ ላይ ጠንካራ አቋም የነበረው ፍቄ መታመሙ ይፋ በሆነበት ወቅት የህዝቡን ርብርብ አስመልክተው ለንባብ ሲበቁ የነበሩት መረጃዎች እንዳመለከቱት ፍቄን ለማዳን ወደ ኋላ ያለ አልነበረም። «የህዝቡ ወደር የሌለው ምላሽ እጅግ የሚያስደስት ነው» በማለት የሚጀምረው ጽሑፍም ይህንኑ በሚያጠናክር መልኩ "የጥበብ ስራን ከማየትና ከማድነቅ በላይ ለተጠባቢው ፍቅርና አክብሮትን የሚለግሰው ውድ ህዝብ አሁንም የጋሽ ፍቃዱን መታመም ከሰማበት ጊዜ ጀምሮ የሰጠው ምላሽ እጅግ የሚያስደስት ነው። በመላው አለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን "ለወገን ደራሽ ወገን ነው" በሚል ከልብ በመነጨ ፍቅር ወገናዊነታቸውን በተግባር እያሳዩ ነው:: በፀሎት ከማሰብ ጀምሮ 'ኩላሊታችንን መለገስ እንፈልጋለን' የሚሉ እና በሀሳብም በገንዘብም የደገፉ በርካቶች ናቸው።"

ሌላው ለተወዳጅነቱ ማሳያ ፍቃዱን "ለኔ ወንድሜ፣ ጓደኛዬ ነው። ከዚያ በላይ አባቴም ነው።" የሚለው፤ የህዝቡን ትብብር በተመለከተ "እግዚአብሔር ይመስገን ከውጪና ከሀገር ውስጥም ከ100 ሰው በላይ ኩላሊት ለመስጠት ፍቃደኛ ሆነ።" በማለት የተናገረው ወንድሙ ግርማ ተክለማርያም "በገዳም ሕግ ገዳም ውስጥ ያረፈ ሰው አስከሬን ከገዳም አይወጣም። ነገር ግን ገዳሙ ትልቅ ትብብር አድርጎልናል። ፍቃዱ የህዝብ ልጅ ነው። ስለዚህ ህዝብ በይፋ እንዲቀብረው አስከሬኑን ሰጥተውናል።" ያለው ነው።

የፍቄን የመጨረሻዎቹን ጊዜያት "ከትንሳኤ በአል በኃላ ወደ ጻበል ሄደ። ጳውሎስ ሆስፒታል ቀጠሮ ላይ ነበር። የቀጠሮው ግዜ እስከሚደርስ 'ቤቴ አልቀመጥም ጸበል ቦታ ገብቼ እግዚአብሄርን እማጸናለሁ' ብሎ ነበር።" በማለት የሚገልፀው፤ ለፍቄ የልጅ አከል የሆነው ዮርዳኖስ "ፍቄ የሀገር ቅርስ ነው። የሀገር ባለውለታ ነው። የሁሉም አባት ነው።" ሲልም ፍቃዱን ከሙያው፤ ሙያውን ካገርና ህዝቡ ጋር አዋህዶ ይገልፃል። ከበቂ በላይ ገንዘብ ተሰባስቧል። እሱም ደስተኛ ነበር። "የሌላ ሰው ኩላሊት ወስጄ ባልተርፍስ የሚል ስጋት ግን ነበረው።" ሲልም ይናገራል።

«የጤና ጥበቃ ሚ/ር አርቲስት ፍቃዱ ተ/ ማርያም በነጻ ሙሉ የኩላሊት ንቅለ ተከላ በሀገር ውስጥ ማድረግ እንዲችል ፈቃድ ሰጥቷል።» የሚለው ዜናም ሆነ፤ በማህበራዊ ሚዲያው ይታይ የነበረው የፍቄን የጤና ሁኔታ እየተከታተሉ የማጋራቱ ተግባር ("ሼር" የማድረጉ) አሁን በህይወት ባለነው ቀርቶ ለመጪው ትውልድም እንደ አዲስ የሚገርም ሆኖ ነው ያለፈው። (በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የቲቢ አምባሳደር ተደርጎ በተሾመበት ወቅት በርካታ ሥራዎችን ለአገሩ ማበርከቱ ይነገርለታል።)

እርግጥ ነው በ1968 ዓመተ ምህረት በሃምሌት ቴአትር ለመጀመሪያ ጊዜ በመሪ ተዋናይነት የመጫወት ዕድል ካገኘባትና ከተጫወተበት ጊዜ አንስቶ የመድረክ ፈርጥ በመሆን በርካታ ቴአትሮችን መጫወቱ የሚነገርለት ፍቃዱን ብዙዎች ብዙ ብለውለታል። ጉዳዩ "ከፈረሱ አፍ" እንዲሉ ነውና ከ"ፋዘር" እንጀምር።

### አቶ ተስፋዬ አበበ (ፋዘር)

የፍቃዱን ከዚህ አለም መለየት ተከትሎ አስተያየታቸውን የሰጡ ብዙዎች ሲሆኑ፤ አንዱም በቅፅል ስሙ የሚታወቀው ፋዘር ነበር። ፋዘር እንዲህ ነበር ፍቄን የገለፀው፡-

በልጅነቱ የሰለጠነው እኔጋ ነበር። ያኔ ሱራፌል ጋሻው ከሚባል ጓደኛው ጋር የመጣው በ1965 ዓ. ም. ነበር። እኔጋ ከመምጣቱ በፊት በትምህርት ቤቱ ሙዚቃ ይጫወት ነበር። ከተዋናይነቱ ባሻገር መለስተኛ ድምጻዊም ነው። እኔጋ ሲመጣ ልጅ ቢሆንም እንደልጅነቱ ሳይሆን ሁሉም ነገር ላይ ይሳተፍ ነበር። በዝማሬና በአጫጭር ድራማ ውስጥም ይገባል። ከእድሜው በላይ የሚያስብ ነበር። ከዛ እሱ፣ ስዩም ተፈራና ሱራፌል ጋሻው ወደ ማዘጋጃ ቤት ሄዱ። በሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን "ቴዎድሮስ" ቴአትር ላይ አጼ ቴዎድሮስን ሆኖ ትልቅ ስራ የሰራ ጀግና አርቲስት ነው። በጣም ግሩም፣ ድንቅና ብርቅ አርቲስት ነበር። የፊልም ኢንዱስትሪው እየተስፋፋ ከመጣ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ትልልቅ ፊልሞች ሰርቷል። በጣም በቅርቡ ደግሞ ከኔ ጋር "መለከት" በተባለ የቴሌቭዥን ድራማ ላይ ይሰራ ነበር። ፍቃዱ በገሀዱ አለም ውስጥ ሰውን አክባሪና ታማኝ ነበር። ለጥበቡ የቆመ ሰው ነበር። ነገር ግን በኩላሊት ህመም ምክንያት ትልቅ አደጋ ደረሰበት። ለህልፈት በቃ። እናም ሁላችንም ሀዘን ተሰምቶናል።

ቴአትር ሲሰራ እውነታን ይዞ፣ እውነታውን አስመስሎ ነው። መስሎ ሳይሆን ሆኖ ነው የሚጫወተው። በተለይ የማደንቀው ቴዎድሮስን ሆኖ ሲጫወት ነው።

አጼ ቴዎድሮስን ሆኖ ሲጫወት ሰውነቱ ሁሉ ይለወጣል። በቃ ፍጹም ቴዎድሮስን ነው የምናገኘው። ቴዎድሮስ በጣም መወደድና አድናቆት ያተረፈበት ስራ ነው። እኔም በጣም የማከብረው የማደንቀው በዚሁ ስራ ነው።

ፍቄ ሩህሩህ፣ ልበ ግልጽ ነው። የታመመ የሚጠይቅ፣ እከሌ ሞተ ሲባል ፈጥኖ የሚደርስም ሰው ነው።

ፍቄ ቁጭ ብለው ሲያዋሩት 'የገበታ አርቲስት ነው'። የሚያመጣቸው ጨዋታዎች ያስፈነድቃሉ። አኩርፎ የመቀመጥ ባህሪ ያለው አይደለም።

ሌላውና ከፍቃዱ ተጠቃሽ ስራዎች አንዱ የሆነው "ጉዲፈቻ" ፊልም ደራሲ ቴዎድሮስ ተሾመም "አባት ነው። አማካሪ ነው። ጓደኛ ነው።" ሲል በወቅቱ ሀዘኑን መግለፁም እዚህ ሊጠቀስ የሚገባው ነው።

### ከመንግሥት ወገንስ?

የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ከፍተኛ የጥናት ባለሙያ መምህር መክብብ ገብረማርያም በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ገልፀውት እንደነበረው፤ አርቲስት ፈቃዱ ተክለማርያም በኢትዮጵያ የቴአትር እና ኪነጥበብ ስራዎች ላይ የጎላ አሻራ አሳርፏል። ለሌሎች ሙያተኞችም አርዓያ በመሆን በስራው አንቱታን ያተረፈ ተዋናይ ነው።

አንጋፋው አርቲስት ፍቃዱ ባደረበት የኩላሊት ህመም ምክንያት የህክምና እና የፀበል ርዳታ ሲደረግለት ቆይቶ ሐምሌ 24 ቀን 2010 ዓ.ም አመሻሽ ላይ በ62 አመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

አርቲስት ፍቃዱ ለበርካታ ዓመታት በነገሰበት የብሄራዊ ትያትር መድረክም የሙያ ባልደረቦቹ፣ ቤተሰቦቹ፣ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት እና አድናቂዎቹ በተገኙበት ከ5 ሰዓት ጀምሮ ለአርቲስቱ አስከሬን የአሸኛኘት መርሃ ግብር ተደርጎለት የነበረ ሲሆን፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶ/ር ወርቅነህ ገበየሁን ጨምሮ ሌሎች የመንግስት ባለስልጣናት፣ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አድናቂቆቹ እና የጥበብ ሰዎች በተገኙበት ሀምሌ 26 ቀን 2010 ዓ.ም በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ስላሴ ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን ቀብሩ ተፈፅሟል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት



ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ፈረሰኞቹ በወዳጅነት ጨዋታ የሱዳኑን ኤል ሜሪክ አሸነፉ

ቦጋለ አበበ

የ2014 ዓም የቤትኪንግ ኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ ቻምፒዮኑ ክለብ ቅዱስ ጊዮርጊስ በአፍሪካ ቻምፒየንስ ሊግ ውድድር ኢትዮጵያን ወክሎ እንደሚሳተፍ ይታወቃል። ፈረሰኞቹ በአፍሪካ ቻምፒዮንስ ሊግ የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታዎችን በአዲስ ዘመን መለወጫ እለት መስከረም 1/2015 ዓ.ም ከሱዳኑ አል-ሂላል ጋር ያደርጋሉ። ለዚህም ከጨዋታው በፊት የተለያዩ የአቋም መፈተሻና የወዳጅነት ጨዋታዎችን ለማድረግ በያዙት እቅድ መሰረት ትናንት ሁለተኛውን የወዳጅነት ጨዋታ ከሱዳኑ አል ሜሪክ ኤስ.ሲ ክለብ ጋር በቢሾፍቱ ክቡር ይድነቃቸው ተሰማ አካዳሚ አድርገዋል። ከእረፍት በፊት በተቆጠሩ ሦስት ግቦች ተጋጣሚያቸውን መርታት የቻሉት ፈረሰኞቹ በጨዋታው አንድ ግብ ብቻ አስተናግደዋል፡፡

አማኑኤል ተርፋ በ24ኛው ደቂቃ፣ ቢኒያም በላይ ደግሞ 41ኛ ደቂቃዎች ላይ በጨዋታ ባስቆጠራቸው ግቦች መምራት የቻሉት ፈረሰኞቹ 42ኛ ደቂቃ ላይ ኢስማኤል ኦሮ አጎሮ ባስቆጠራ የፍፁም ቅጣት ምት ግብ መሪነቱን ይዘው የመጀመሪያውን የጨዋታ ክፍለጊዜ አጠናቀዋል፡ ፡ በሁለተኛው አጋማሽ ፈረሰኞቹ ሌሎች ግቦችን ያክላሉ ተብሎ ቢገመትም የኤል ሜሬክን መረብ ዳግም መድረፍ አልቻሉም፡፡ ተጋጣሚያቸው በአንፃሩ ከመጀመሪያው አጋማሽ የተሻለ እንቅስቃሴ በማድረግ 55ኛ ደቂቃ አካባቢ በዜሮ ከመሸነፍ ያዳነችውን ግብ ማስቆጠር ችሎ ጨዋታው 3ለ1 በሆነ ውጤት ተጠናቋል፡፡



ፈረሰኞቹ የሱዳኑን ኤል ሜሪክ በወዳጅነት ጨዋታ ገጥመው 3ለ1 በሆነ ውጤት አሸንፈዋል፣

ፈረሰኞቹን በምክትል አሰልጣኝነት እየመሩ ለቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየርሊግ ቻምፒዮንነት ክብር ያበቁት አሠልጣኝ ዘሪሁን ሸንገታ ከቀናት በፊት የክለቡ ዋና አሰልጣኝ ሆነው መሾማቸው የሚታወስ ሲሆን ለቻምፒዮንስ ሊጉ ዝግጅታቸውን በቢሾፍቱ ይድነቃቸው ተሰማ አካዳሚ እያደረጉ ይገኛሉ። ፈረሰኞቹ ከሳምንት በፊትም የመጀመሪያ የአቋም መፈተሻ ጨዋታውን ወደ ታንዛኒያ በማምራት ከሲምባ ጋር አከናውነው የሁለት ለዜሮ ሽንፈት ገጥሟቸዋል።

በቻን አፍሪካ ዋንጫ ለመሳተፍ የመጨረሻው የማጣሪያ ምእራፍ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ዋልያዎቹ) ከሩዋንዳ አቻቸው ጋር ለሚያደርጉት ወሳኝ ጨዋታ በአሰልጣኝ ውበቱ አባተ ስብስብ ውስጥ ተካተው ዝግጅታቸውን በታንዛኒያ እያደረጉ ከሚገኙ የፈረሰኞቹ ተጫዋቾች መካከል አብዛኞቹ በትናንቱ የወዳጅነት ጨዋታ መሰለፋቸው ታውቋል። ከነዚህም መካከል ጋቶች ፓኖም ፣ ቸርነት ጉግሳ፣ ሄኖክ አዱኛ፣ ሱሌይማን ሀሚድ፣ ረመዳን የሱፍ እና ምኞት ደበበ ከታንዛኒያ ተመልሰው ፈረሰኞቹን ተቀላቅለዋል። ከውል ማደስ ጋር ተያይዞ እስካሁን በፈረሰኞቹ መለያ መቆየቱ ያልተረጋገጠው የአጥቂ ስፍራ ተጫዋቹ አማኑኤል ገብረሚካኤል ግን ከታንዛኒያ መጥቶ ፈረሰኞቹን እንዳልተቀላቀለ ዘገባዎች አመልክተዋል።

የሱዳኑ ክለብ ኤል-ሜሪክ በአፍሪካ ቻምፒየንስ ሊግ የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታ ከጅቡቲው አርታ ሶላር ጋር የሚያደርገውን የሜዳው ላይ ጨዋታ በባህርዳር ስቴድየም ለማድረግ መወሰኑን ተከትሎ ነው ትናንት ከፈረሰኞቹ ጋር የወዳጅነት ጨዋታ ለማድረግ የቻለው። አልሜሪክ ለአቋም መፈተሻ ጨዋታው ከቀናት በፊት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ዝግጅት አድርጓል። ሌላኛው የሱዳኑ ክለብ አል-ሂላል ኡንዱርማን ላይ አል-ሂላል ስታዲየምን ለመጠቀም ካፍ ፍቃድ ቢሰጠውም የከተማው ተቀናቃኝ ክለብ ሜሪክ ግን እንዲጠቀምበት አለመፈለጉን ተከትሎ ሜሪክ የሜዳ ላይ ጨዋታውን ከሀገር ውጪ ለማከናወን ግዴታ ውስጥ ገብቷል። ይህንን ተከትሎም ክለቡ የባህር ዳር ስታዲየምን ለመጠቀም እንደወሰነና ለካፍ እንዳሳወቀ ይታወሳል። ሜሪክ በባህር ዳር ስታዲየም ጨዋታውን የሚያደርገው መስከረም 7/2015ዓ.ም ነው።

የቀጣዩ ዓመት የአፍሪካ ቻምፒየንስ ሊግ እና ኮንፌዴሬሽን ካፕ ውድድር የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታዎች ከቀናት በኋላ መደረግ ይጀምራሉ። የሀገራችን ተወካዮች ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ፋሲል ከነማም ለውድድሮቹ እየተሰናዱ የሚገኙ ሲሆን የሜዳ ላይ ጨዋታቸውንም በባህር ዳር ስታዲየም እንደሚያከናውኑ ይፋ መሆኑ ይታወሳል።

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በ2022/23 የውድድር ዘመን የካፍ ቻምፒዮንስ ሊግ እና ካፍ ኮንፌዴሬሽን ዋንጫ የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታዎች ፍቃድ ያገኙ ስታዲየሞችን ዝርዝር ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ቀደም ሲል አሳውቋል።

ካፍ ፍቃድ ያገኙ የ39 ሀገራት ስታዲየሞችን በላከበት ዝርዝር ላይ ከኢትዮጵያ የባህር ዳር ዓለምአቀፍ ስታዲየም ፍቃድ ማግኘቱ የተገለፀ ሲሆን በዚህም መሰረት በቻምፒየንስ ሊጉ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከሱዳኑ አል ሂላል፣ በኮንፌዴሬሽን ዋንጫው ፋሲል ከነማ ከቡሩንዲው ቡማሙሩ ክለብ ጋር የሚያደርጓቸው ጨዋታዎች ባህር ዳር ስታዲየም ላይ የሚከናወኑ ይሆናል።

ካፍ ከላከው ዝርዝር ጋር በላከው መግለጫ ይህ ፈቃድ የሚያገለግለው ለቅድመ ማጣሪያ ጨዋታዎች መሆኑን በማውሳት ለምድብ ጨዋታዎች ግን በድጋሚ ግምገማ እንደሚያደርግ ታውቋል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# እንኳን ለ፳፻፲፭ (2015)ዓ.ም አዲስ አመት የዘመን መለወጫ አደረሳችሁ!

ባህል በዘመናችን በበርካታ የዓለም አገራት የሕዝቦች ማንነት መገለጫ በመሆን ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እያሳየ መጥቷል፡፡ በተለይም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በባህል የተለያዩ ሕዝቦች በሚኖሩባቸው አገሮች ባህል ያለው ቦታ እጅግ የጎላ ነው፡፡ ለዚህም ዓለም በሉላዊ አስተሳሰብ (በግሎባላይዜሽን) ወደ ጠባብ መንደር እየተለወጠች መምጣቷና የሕዝቦች ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴም በፍጥነት ማደጉ የቱባ ባህል፣ ቋንቋና እምነት ባለቤት ለሆኑ አገራት ከባህል ዘርፍ በርካታ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ልዩ ዕድል አላቸው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያም በርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ እንደ መሆኗ የበርካታ ባህላዊ እሴቶች እና ቋንቋ ባለቤት እንድትሆን አስችሏታል፡፡ ይህም እንደሌሎች የዓለም አገራት የባህልን ዘርፍ በአንድ አገር ገጽታ ግንባታ ባሻገር ባህልን የኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አጉልቶ በማውጣት ለማጣጣም ተስፋ ሰጪ ያደርጋታል፡፡

ከዘርፉ የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የአስር ዓመት ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮችን ቀርጾ በመሥራት ላይ ይገኛል፡



፡ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በብዝኃ ባህላዊ ሀብቶችን በማልማት፣ የጥበብና ፈጠራ ሥራዎችን በማዘመን ተደራሽነትን ማረጋገጥ ሁለንተናዊ የማኅበረሰብ እድገት ለማምጣት የተጠበቁና የለሙ ባህላዊ ሀብቶችን ለትውልድ ለማሸጋገር ያልተበረዘ ባህል፣ የሕዝቦች እንግዳ ተቀባይነት፣ ተስማሚ የሆነ የአየር ንብረትና መልክዓምድራዊ አቀማመጥ ያላት የብዝኃ ባህል አገር ስትሆን ከሌላው የዓለም ክፍል ልዩ የሚያደርጋት ይኸው ነው፡፡

በአራቱም ማዕዘናት የበርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ስብጥር የሚታይባት አገራችን በእያንዳንዱ ብሔረሰብ ውስጥ ልዩ የሆነና አግራሞትን የሚጭር ባህላዊ አለባበስ፣ የአመጋገብ ሥርዓት፣ ባህላዊ ጭፈራ፣ በዓላት አከባበር፣ ወዘተ ባለቤት ነች፡፡ መሆኑም አገራችን ኢትዮጵያ በብዝኃ ባህሎቿና በባህላዊ የእርቅ ሥርዓቷ ቀደምትነት ያላት ስትሆን በዘርፉ ብዙ ያልተዳሰሱ እምቅ የባህል ሀብቶችን በውስጧ የያዘች እንደመሆኗ መጠን ለዚህም ማሳያ በቋንቋ፣ በአገር በቀል ዕውቀት፣ በባህላዊ እሴቶች፣ በኪነ ጥበብ፣ በሥነጥበብ፣ በሥነፁሑፍ እና በእደጥበብ እጅግ ሰፊ የሆኑ እምቅ ሀብት ያላት ናት፡፡

ለአገራችን ኢትዮጵያ ሰላም፣ ፍቅር፣ መተሳሰብን ያብዛልን! በዓሉ የመተሳሰብ ሰላም እና ፍቅር ይሁንልን፡፡

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር**
**እንኳን ለ፳፻፲፭(2015)ዓ.ም አዲስ አመት አደረሳችሁ!**

Telegram https://t.me/ministry ofcultureandtourism
Facebook https://www.facebook.com/cultureandsportethiopia